# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 228 ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## “የኢትዮጵያ አየር ኃይል የኢትዮጵያ ከፍታ ማሳያ ነው”

- ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ
የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም

ጌትነት ምህረቴ

ቢሾፍቱ፡- የኢትዮጵያ አየር ኃይል የኢትዮጵያ ከፍታ ማሳያ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ፡፡

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ በትናንትናው እለት በኢትዮጵያ አየር ኃይል ቅጥር ግቢ ውስጥ በተካሄደ የፎቶ አውደ ርዕይና “ሰማዩ የእኛ ነው” የተሰኘ የፊልም ምርቃት ስነ ስርዓት ላይ እንደገለፁት፤ አሁን እየተገነባ ያለው የኢትዮጵያ አየር ኃይል የኢትዮጵያ ከፍታ ማሳያ ነው።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ እንደገለጹት፤ ባለፉት አራት አመታት የሪፎርም ስራ ከተሰራባቸው የመከላከያ ተቋማት ውስጥ አንዱ አየር ኃይል ነው፡፡ በዚህም ተቋሙ ለሀገር በሚመጥን ደረጃ የለውጥ ስራዎችን አከናውኗል፡፡

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዛሬ ሱ 27 ዘመናዊ ተዋጊ ጀትን ጨምሮ ሌሎች ተዋጊ ጀቶችና ሄሊኮፕተሮች እዚሁ የሚጠገኑበትን አቅም አዳብሯል ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ የዕድገት ጎዳና ላይ ይገኛል ብለዋል።

ለውጡ ካስገኛቸው ፍሬዎችም አንዱና ቀዳሚው አየር ኃይል መሆኑን የጠቀሱት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በአስተማማኝ መልኩ የሚጠብቅ ሀገራዊ ሠራዊት እየተገነባ ነው፤ ይህን ስራ የፊልም ባለሙያዎች በማስተዋወቅ ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዥ ሌተናል ጀነራል ይልማ መርዳሳ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ አንጋፋው

“የኢትዮጵያ አየር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የአማራ ክልል ከሱዳን ተፈናቅለው ወደክልሉ ለገቡ ዜጎች ድጋፍ እያቀረበ ነው

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- በሱዳን ሰሞኑን በተከሰተው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ተፈናቅለው ወደ ክልሉ እየገቡ ላሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ሰብአዊ ድጋፍ ለማቅረብ እየሰራ መሆኑን የአማራ ክልል አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሱዳን ሰሞኑን በተከሰተው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ከሱዳን ወደ አማራ ክልል ተፈናቅለው እየገቡ ላሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ሰብአዊና ቁሳዊ ድጋፍ ለማድረግ የሎጅስቲክና የተለያየ ኮሜቴ ክልሉ አዋቅሮ እየተሰራ ነው፡፡



አቶ ግዛቸው ሙሉነህ

ባለፉት አምስት ቀናት በምዕራብ ጎንደር ዞን በሺህ የሚቆጠሩ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ከሱዳን በጦርነቱ ምክንያት ተፈናቅለው ወደ ክልሉ መግባታቸውን አቶ ግዛቸው ገልጸዋል፡፡

ከሱዳን ተፈናቅለው ወደ አማራ ክልል ከገቡት የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ውስጥ ህፃናት፣ ሴቶች፣ እናቶችና አዛውንቶች እንደገኙበት ጠቁመዋል፡፡

ከሱዳን ወደ ክልሉ ከሚገቡ ተፈናቃዮችም መካከል ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንደሚገኙበት ተናግረዋል።፡

ተፈናቅለው እየገቡ ያሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎችን በጊዜያዊ መጠለያ ለማቆየት ክልሉ የተለያዩ ኮሚቴዎችን አዋቅሮ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

የአማራ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














### ፍርድ ቤቱ በሽብር ወንጀል በተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ የ14 ቀናት የምርመራ ጊዜ ፈቀደ

ገጽ 4




ዜና

# አደንዛዥ እጾች በወጣቶች ላይ ከፍተኛ ችግሮችን እያስከተሉ ነው

መዓዛ ማሞ


ወ/ሮ ሙና አህመድ

አዲስ አበባ፡- አደንዛዥ እጾች እና አሉታዊ መጤ ልማዶች በወጣቶች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠሩ መሆኑን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ በአንጻሩ እጾቹ እና መጤ ልማዳዊ ድርጊቶቹ በሚያስከትሉት ጉዳት ላይ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችም በቂ አለመሆናቸው ተጠቁሟል፡፡

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ ሙና አህመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአደንዛዥ እጾች እና አሉታዊ መጤ ልማዶች በወጣቶች ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ችግሮች እያስከተሉ ነው፡፡

ወጣቶች አደንዛዥ እጾችን መጠቀም እንዳይጀምሩ መከላከልን መሰረት በማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም የችግሩ ስፋት እየጨመረ በመምጣቱ ቀጣይነት ያለው የቅንጅት ስራ ሊሰራ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

የአደንዛዥ ዕጾች መከላከል ስራዎች አፈጻጸም ሲገመገም ትልቅ የቅንጅት ክፍተት መኖሩ በጥናት መረጋገጡን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የተጀመሩ ስራዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ አለመሰራታቸው ወጣቱን በተፈለገው ደረጃ ለመታደግ አዳጋች እንዳደረገው ተናግረዋል፡፡

እንደ ወ/ሮ ሙና አህመድ ገለጻ፤ ወጣቶች አደንዛዥ እጾችን መጠቀም እንዳይጀምሩ መጀመሪያ መከላከልን መሰረት በማድረግ ስራዎች መሰራት አለባቸዉ፡፡ የመከላከል ስራውን ትምህርት ቤቶች፣ዩኒቨርሲቲዎች፣የጤና እና የፍትህ ሴክተሮች በጋራና በቅንጅት በመስራት ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡

የጭፈራ ቤቶችን መቀነስ እንዲሁም አደንዛዥ ዕጽ እና አልኮል የሚጠቀሙ ወጣቶችን መታደግ የሚቻለው የጋራ ጥረት ሲደረግ እንደሆነ የጠቆሙት ወ/ሮ ሙና፤ ትምህርት ቤቶች ላይ በተማሪዎቹ እድሜ ልክ የሚሰጥ ስልጠና መኖር እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ወጣቶች ስብዕናቸው የተገነባ፣ አገር ወዳድ እና ኃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ የስብዕና ግንባታ ማዕከላት እጅግ አስፈላጊ ናቸው ያሉት ወ/ሮ ሙና፤ እንደ አገር ከ3 ሺህ በላይ ማዕከላት ቢኖሩም በትክክል ስራ ላይ ያሉት 1ሺህ 545 ብቻ በመሆናቸው ሁሉም ወደ ስራ እንዲገቡ መሰራት አለበት ብለዋል፡፡

ማዕከላቱ ወጣቱን ስልጠና እና መረጃ በመስጠት እንዲሁም ስራዎችን በመስራት ረገድም እኩል እንዳልሆኑ ጠቁመው፤ ትምህርት ቤቶች ወጣት ተማሪዎችን በመያዛቸው የተማሪዎች ስብዕና የሚገነባባቸው ክበባት ሊኖራቸው እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

ወ/ሮ ሙና እንደሚሉት በመጀመሪያ መከላከል ላይ መስራት እንዲሁም አደንዛዥ ዕጽ በመጠቀም ችግር ውስጥ የገቡት ደግሞ ከሱስ እንዲላቀቁ ማከሚያ ማዕከላትን መገንባት ያስፈልጋል፡፡

በሱስ የተጠቁ ወጣቶች ከሱስ እንዲላቀቁ እና የስነ ልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ የመልሶ ማገገሚያ በመገንባት ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ትልቅ ምሳሌ እንደሆነ ተናግረው፤ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም የመልሶ ማገገሚያ ማዕከላትን በማቋቋም ችግሩን ለመቅረፍ መስራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

የወጣት አቅም በሌለበት የምናስበውን ብልጽግና ማምጣት አንችልም ያሉት ወ/ሮ ሙና፤ የወጣቶችን አቅም መጠቀም የሚቻለው ወጣቶች ጤነኛ ሲሆኑ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ ላይ ተቀናጅተው እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በዘጠኝ ወራት ከ250 ሺህ ዩኒት በላይ ደም ተሰበሰበ

ሄለን ወንድምነው


አቶ ሀብታሙ ታዬ

አዲስ አበባ፡- በዘጠኝ ወር ውስጥ 250 ሺህ 235 ዩኒት ደም መሰብሰብ መቻሉን የኢትዮጵያ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 በመላው ኢትዮጵያ በዓመት 490 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዷል። በዘጠኝ ወራት ውስጥ 250 ሺህ 235 ዩኒት ደም ተሰብስቧል።

አቶ ሀብታሙ እንዳሉት፤ በዘጠኝ ወር ውስጥ 343 ሺህ 223 ዩኒት ደም እንደሚሰበሰብ ታቅዶ ነበር፤ ይሁንና የደም ለጋሾች ተሳትፎ በተወሰኑ ወራት እና ክልሎች ዝቅተኛ በመሆኑ ከዕቅድ በታች አፈጻጸም እንዲመዘገብ ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ጾም ላይ በመሆናቸው፣ በበዓላት መደራረብ እና በክረምት ወቅት ትምህርት ቤቶች ዝግ በመሆናቸው፤ ወቅቱ ቅዝቃዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ደካማ የደም ልገሳ አፈጻጸም የታየበት መሆኑንም አቶ ሀብታሙ አንስተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ዘመቻዎች አማካኝነት የደም ልገሳ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው ቢቀጥሉም በሚፈለገው ልክ መሰብሰብ አልተቻለም ብለዋል፡፡

የደም ልገሳ ባህሉን ለማዳበር በተለይ በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ሃይማኖት ተቋማት፣ የደም ልገሳ ክበቦች እና ማህበራት ጋር የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቅናቄ ስራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል፡፡ የተጀመሩትን የንቅናቄ ስራዎች በሁሉም አካባቢዎች ማስፋት እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

በክልል ደረጃ ያለውን የደም ልገሳ አፈጻጸም በተመለከተ የተወሰኑ ክልሎች ላይ በበጀት እጥረት ምክንያት ደካማ እንቅስቃሴ መኖሩን የተናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ በአዲስ አበባ፣ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ተናግረዋል። በአንጻሩ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ላይ ደግሞ የደም ልገሳ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው ብለዋል።

ክልሎች ላይ ለደም ባንክ የሚሰጠው ትኩረት ከሌሎች የጤና ሴክተሮች ዝቅ ያለ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ የበጀት እጥረት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ልክ መስራት አይችሉም፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት ዝቅተኛ አፈጻጸም ባለባቸው ክልሎች ከጤና ሚኒስቴር እና ከአካባቢው ጤና ቢሮዎች ጋር በጋራ መስራት የሚያስችላቸውን ሁኔታ እያመቻቹ እንደሚገኙ አስታውቀዋል፡፡

የደም ልገሰው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥል ማዕከል ላይ እየተሰራ ያለው ስራ አበረታች ቢሆንም፣ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር እና ሁሉም ማህበረሰብ የደም ልገሳ ስራውን ባህል አድርጎ መቀጠል እንዲችል በትኩረት ሊሰራ ይገባል ብለዋል፡፡

የደም ማሰባሰብ ስራ ላይ በርካታ ችግሮች ያጋጥማሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ሰዎች መስፈርቱን በደንብ ካለማወቃቸው የተነሳ ደም ለመለገስ መፍራታቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት እንደሚገባ የሚያመላክት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በየዓመቱ የደም ተጠቃሚዎች እና ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚያድግ የደም ልገሳ ባህል መኖር እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ባሳለፍናቸው ወራት የእስልምናና ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ጾም ላይ በመቆየታቸው እና በዓላት በመደራረባቸው ምክንያት የደም ለጋሾች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነሱ ምክንያት በቂ ደም አለመኖሩን ገልጸው፤ ማህበረሰቡ ደም እንዲለግስ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ኢትዮጵያና ታንዛኒያ የታዳሽ ኃይል የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ እንደሚሰሩ አስታወቁ

ማርቆስ በላይ



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ታንዛኒያ በታዳሽ ኃይል የጋራ ተጠቃሚ ለመሆን እንደሚሰሩ አስታወቁ፡፡ ለሁለት ቀናት የሚካሄደው “አፍሪካ ኢነርጂ ናው 2023” የተሰኘው በኢትዮጵያና ታንዛኒያ መካከል በታዳሽ ኃይል የኢንቨስትመንት ዕድሎች ዙሪያ የሚመክረው መድረክ ትናንት በአዲስ አበባ ተጀምሯል።

በወቅቱ የኢትዮጵያ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ታንዛኒያ እንዲሁም የተለያዩ በታዳሽ ኃይል ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች በጋራ ለመስራት መግባባት የሚያደርጉበት መድረክ ተፈጥሯል።

ኢትዮጵያና ታንዛኒያ በዘርፉ ያላቸውን አቅም በጋራ ለማሳደግና የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ መልካም ዕድል የሚፈጥር ውይይት እየተካሄደ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ጨምሮ የተለያዩ ኢንቨስትመንት ተቋማት እየተሳተፉ ይገኛሉ ያሉት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ በኢትዮጵያና በታንዛኒያ የሃይል ማመንጫ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ተቋማት የልምድ ልውውጥ እያደረጉ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

አፍሪካ ትልቅ የሆነ ታዳሽ ሀይል ሀብት ያለባት አህጉር ናት ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሌላ በኩል ከፍተኛ የሆነ የገንዘብና የቴክኖሎጂ ችግር ያለባት በመሆኑ ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም፡፡ በኢትዮጵያ ከሚገኘው የታዳሽ ሀይል ሀብት መልማት የቻለው አነስተኛ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በመሆኑም መድረኩ ገንዘብና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ልምድን በማስተባበር በዘርፉ የተሻለ ስራ ለማከናወን ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በውሃ፣በንፋስና በፀሀይ ኃይል ሃብት ትልቅ አቅም ያላት መሆኑን ጠቁመው፤ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የሌሎች ሀገራት ኢንቨስተሮችን መሳብ ያስፈልጋል፡፡ ሰፊ ልማት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ከታንዛኒያ ኢንቨስተሮች ጋር በቅርበት ለመስራት ዝግጁ ነን ብለዋል።

እንደ ኢንጂነር ሀብታሙ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በታዳሽ ኃይል አማራጮች ከ400 ጊጋ ዋት በላይ ኤሌክትሪክ የማምረት አቅም አላት። ሆኖም እስካሁን የሚመረተው 5 ነጥብ 1 ጊጋ ዋት ብቻ ነው። የዓባይ ግድብ ፕሮጀክት ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ደግሞ የምርት መጠኑን ለማሳደግ ይረዳል፡፡

ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ለአጎራባች ሀገራት በማሰራጨት ላይ ትገኛለች ያሉት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ በዚህ ረገድ ባለሀብቶች ኢንቨስት ለማድረግ የሚረዳቸው መሰረተ ልማት ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል።

የታንዛኒያው የጂኦተርማል ልማት ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ማቲው መዋንጎምባ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያና ታንዛኒያ ሰፊ ታዳሽ ኃይል ሀብት አላቸው። ሁለቱ አገራት ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት በዘርፉ የሚኖራቸውን ትብብር ማጠናከር አለባቸው፡፡

እንደ ኢንጂነር ማቲው ገለጻ፤ መድረኩ ታንዛኒያና ኢትዮጵያ ያላቸውን ዕምቅ የታዳሽ ሀይል ሀብት ለማሳደግ የሚያስችል ነው፡፡ በልምድ ልውውጥና በጋራ ትብብር የሚከናወኑ የታዳሽ ኃይል ልማቶችን ለማሳደግ ውይይቱ ጠቃሚ ነው።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና የተለያዩ የውጪ ሀገራት ባለሀብቶች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡

ዜና

# ከታክስ ነጻ ንግድ መፈቀዱ የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ እንዳይባባስ አወንታዊ ሚና ተጫውቷል

**ዘላለም ግዛው**



ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ

አዲስ አበባ፡- ምርቶች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ መፈቀዱ የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ አወንታዊ ሚና መጫወቱን የጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ መንግስት የሕብረተሰቡን ኑሮ ለመደጎም ባለፉት አምስት ዓመታት ሊሰበስብ ይገባ የነበረውን ከ80 ቢሊዮን ብር በላይ ቀረጥና ታክስ በመተው በፍራንኮ ቫሎታ መብት መሰረታዊ የምግብ ፍጆታዎች እንዲገቡ ማድረጉም ተጠቁሟል፡፡

ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 80 ቢሊዮን ብር መንግስት መሰብሰብ የነበረበት ገቢ እንጂ አጠቃላይ የእቃዎች ዋጋ አይደለም ያሉት አቶ ደበሌ፤ ትግበራው የህብረተሰቡ የኑሮ ቀውስ እንዳይባባስ አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ ገበያውን፣ ህብረተሰቡንና የንግድ ስርዓቱን አግዟል ብለዋል፡፡

መሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎችን በፍራንኮ ቫሉታ እንዲገቡ መንግሥት ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት የገጠመውን የምግብ ፍጆታ ለመቅረፍና ሕብረተሰቡን ለማገዝ ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብ ለህብረተሰብ ፍጆታ እንዲተው ተደርጓል። መንግስት ቀረጥ ቢሰበስብ ኖሮ ከ80 ቢሊዮን ብር በላይ ይሰበስብ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

ይህንን ያህል የምግብ ፍጆታ ገብተው ለሕብረተሰብ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ አገራዊ የምግብ ቀውስ በከፍተኛ ደረጃ ሊባባስ፣ ግሽበቱም ወደ ከፍተኛ ግሽበት ሊሸጋገር ይችል እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ እያደገ የመጣውን የዋጋ ንረት መሠረት በማድረግ በገንዘብ ሚኒስቴር ውሳኔው የተላለፈ ሲሆን፤ ፍቃዱ ቀላል የማይባል ጥቅም አስገኝቷል ብለዋል አቶ ደበሌ። ይሁን እንጂ በተባለው ልክ የኑሮ ውድነቱን እንዳልቀነሰ አመልክተዋል፡፡

አገራዊ የምርታማነት አቅም ከፍላጎቱ አኳያ ተመጣጣኝ አለመሆኑ ለኑሮ ውድነቱ አለመቀነስ አንድ ምክንያት መሆኑን ያነሱት አቶ ደበሌ፤ በርግጥ ይህ የኑሮ ውድነቱን ከነአካቴው ላይቀንስ ይችላል፣ ከፍተኛ ምርት አምርተናል ያሉ አገራት በምግብ እጥረት እየተናወጡ ናቸው ብለዋል፡፡

አቶ ደበሌ እንደተናገሩት፤ አገራዊ የምርታማነት አቅም የኑሮ ውድነቱን ሊቆጣጠር የሚያስችል አለመሆኑ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ምክንያት ካደረጉ ጉዳዮች ይጠቀሳል። መፍትሄው ምርታማነት መጨመር መሆኑ ታምኖበት እየተሰራ ይገኛል። ስንዴን በከፍተኛ ደረጃ አምርቶ የምግብ ፍጆታን መሸፈንና ለውጭ ገበያ ማቅረብ አንዱ ተግባር ነው፡፡

በፍራንኮ ቫሉታ መብት ለህብረተሰቡ የተተወውን፣ ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበበትን እቃ አስገብተው መንግስት በተወው ልክ ታምነው ለሕብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸው የነበሩ የምግብ ፍጆታዎችን አስመጥተው የሚነግዱ አካላት ታማኝ አለመሆን ትልቅ አደጋ ነው ብለዋል።

አቶ ደበሌ እንዳሉት፤ እያንዳንዳቸውን ተከታትሎ መቆጣጠር ያስቸግራል፡፡ አለመታመናቸውና ትርፍን አላግባብ ከማጋበስ የሚመነጭ ስሜት ሕብረተሰቡ ላይ ጫና አደርሷል፣ ኑሮ ውድነቱንና ቀውሱን በማባባስ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በዞን፣ በክልልና በፌዴራል ደረጃ የሚቆጣጠሩና የንግዱን ስርዓት የሚመሩ አካላት እቃዎቹ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ወደ ማሕበረሰቡ እስኪደርሱ ያለውን ሂደት የመከታተልና የመቆጣጠር ክፍተት አለ ሲሉም ጠቅሰዋል፡፡

የተሟላ መረጃ ወስደው ያለመታከት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በህገወጥ መንገድ ንግድ የሚያጋብሱትን ስርዓት ያለማስያዝና ተጠያቂነትን ያለማስፈን የችግሩ ተደማሪ ሆኖ የኑሮ ውድነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲባባስ አድርጓል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የውጭ ምንዛሬ እጥረትም በዚህ ማዕቀፍ ሊታይ ይችላል ያሉት ኃላፊው፤ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር፣ የውጭ ምንዛሬ በማሳደግ የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም መስራት እንደሚገባም አመልክተዋል፡፡

የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ እና በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ሳይጠየቅ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ መሠረታዊ የሚባሉት የምግብ ሸቀጦች በፍራንኮ ቫሉታ እንዲገቡ ከተፈቀዱት መሠረታዊ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች መካከል ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር የሕፃናት ወተትና ሩዝ ይገኙበታል፡፡

# ወጣት ስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፍ የቢዝነስ ማበልጸጊያ ፕሮጀክት ወደስራ ገባ

**ሄለን ወንድምነው**



ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ



አቶ ንጉሱ ጥላሁን

አዲስ አበባ፡- ወጣት ስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፍ የቢዝነስ ማበልጸጊያ ፕሮጀክት ወደስራ ማስገባቱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት (አዲስ ቻምበር) አስታወቀ፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ ማዕከሉ ይፋ በሆነበት ወቅት እንደገለጹት፤ ምክር ቤቱ ከልማት አጋሮቹ ጋር በመተባበር የግሉን ዘርፍ ለማጠናከርና የወጣቶችን ስራ ፈጣሪነት ለማሳደግ የሚረዳ ፕሮጀክት በስራ ላይ አውሏል።

ፕሮጀክቱ ስራ ፈጣሪ ወጣቶች ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ የሚረዳ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ወጣቶች የንግድ ስራቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዱ የፋይናንስ ድጋፎችን ለማቅረብ የሚረዳ ፕሮጀክት መሆኑንም ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ በስራ ላይ ላሉና ለጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች ስልጠና የመስጠት፣ የገበያ ትስስር የመፍጠር፣ የፋይናንስ አቅማቸውን የማጠናከርና የስራ ፈጣሪነት ባህልን የማሳደግ ዓላማ ያለው መሆኑን ወይዘሮ መሰንበት ገልጸዋል።

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት እንዳስታወቁት፤ እንደሀገር የተያዘውን ዘላቂ ልማት የማረጋገጥ ግብ ለማሳካትና የቢዝነስ ምህዳሩን ለማስፋት የሚረዳ ፕሮጀክት በመሆኑ ወጣቶች በስፋት ሊጠቀሙበት ይገባል።

የወጣቶች ስራ ፈጠራ ማበልጸጊያ ፕሮጀክቱ ለአራት ዓመታት እንደሚተገበር የገለጹት ወይዘሮ መሰንበት፤ ማዕከሉ ከ500 በላይ ወጣቶችን ተሳታፊ ያደርጋል፤ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ተይዟል ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር ወጣቶችና አዲስ ስራ ጀማሪዎች እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በፈጠራ ማዕከሉ በአጋርነት እንዲሰሩ ያደርጋል፤ መካከለኛና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለማቃለል ትኩረት ተደርጓልም ሲሉ አስረድተዋል።

የስራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ምክር ቤቱ ወደስራ ያስገባው የቢስነስ ማበልጸጊያ ፕሮጀክት ወጣቶች በስራ ፈጠራው ዘርፍ በተሻለ ሁኔታ እንዲጠናከሩ የሚረዳ ነው።

ወጣት ስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፈው የቢዝነስ ማበልጸጊያ ፕሮጀክቱ ውጤታማ እንዲሆን የስራና ክህሎት ሚኒስቴር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል፡፡

ስራ ፈጣሪዎችን ስኬታማ ማድረግ ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ማደግ ትልቅ ሚና ይኖረዋል ያሉት አቶ ንጉሱ፤ ፕሮጀክቱም እንደሀገር ለተያዘው ውጤታማ የስራ ፈጠራ ግብ አስተዋጽኦ ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በፕሮጀክቱ ሂደት ለወጣት ስራ ፈጣሪዎች እንዲሁም ለመካከለኛና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የክህሎት፣ የቴክኒክና የፋይናንሻል ድጋፎችን በተጠናከረ መልኩ መስጠት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

# ከ250 በላይ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት የንግድ ትርኢት ሊካሄድ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ከ250 በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት 13ኛው ኢትዮ ቻምበር አለም አቀፍ የንግድ ትርኢት በአዲስ አበባ ሊካሄድ መሆኑን የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሚያዘጋጁት የንግድ ትርኢት በርካታ የሀገር ውስጥ አምራቾችና ስምንት ከሚሆኑ የውጭ ሀገሮች የተወጣጡ ኩባንያዎች ይሳተፉበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ገልጸዋል፡፡

የንግድ ትርኢቱ “የኢትዮጵያን ይግዙ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያድርጉ” በሚል መሪ ቃል ከሚያዝያ 19 እስከ 23 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማእከል ይካሄዳል፡፡

አቶ ውቤ የንግድ ትርኢቱ የኢትዮጵያ ምርቶች አገልግሎቶችና ግብአቶችን በማስተዋወቅ ፣ ለኢንዱስትሪ ልማት እድገት፣ ለስራ ፈጠራ ፣የገበያ ትስስር ላይ ሚና ይኖረዋል ያሉ ሲሆን፤ በተለይም የውጭ የንግድ ማእከላት መሳተፋቸው ለሀገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶች የሚሆን ግብአቶች ፣ቴክኖሎጂዎች የሚተዋወቁበትና የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ደረጃ በማስተዋወቅ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በአትዮጵያ ምርታማነት እምብዛም ነው ያሉት አቶ ውቤ፤ ከአለም አቀፍ የንግድ ማእከላት ቴክኖሎጂንና ሌሎች ጠቃሚ ልምዶችን በመውሰድ ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

ለስምንት ቀናት በሚቆየው የንግድ ትርኢት ከአለም አቀፍ የንግድ ተቋማት እና የሀገር ውስጥ ኢንተርፕራይዞች ምርቶችና አገልግሎቶች የሚቀርቡበት ሲሆን፤ ከሌላው ጊዜ በተለየ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሳተፉበት ነው ብለዋል፡፡

በዚህም ከሀገር ውስጥ 40 በመቶ የሚሆኑት ከአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሳተፉበት ሲሆን ቀሪው 60 በመቶ ከፍተኛ አምራቾች ይሳተፉበታል።

እንደ አቶ ውቤ ገለጻ ከመላው አገሪቱ የተወጣጡ ኢንተርፕራይዞች ተሳታፊ የሚሆኑበት ይህ የንግድ ትርኢት ከውጭ የንግድ ማእከላት ጋር መካሄዱ ለልምድ ልውውጥና የገበያ ትስስር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ከንግድ ትርኢቱ በተጨማሪም የአቻ ለአቻ የንግድ መድረክ ይዘጋጃል፡፡ በዚህ መድረክም የንግድ ማህበረሰቡ የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ተሞክሮ ማግኘት የሚያስችል ስራ እንደሚሰራ አቶ ውቤ ገልጸዋል፡፡

የንግድ ትርኢቱ ሲከፈት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ የተለያዩ አምባሳደሮች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ይገኛሉ፡፡




# ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023 ከዛሬ ጀምሮ በአዲስ አበባ ይካሄዳል

## - ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት እንደሚስብ ይጠበቃል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያስችል ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2013 የተሰኘ ፎረም ከዛሬ ጀምሮ በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳሳወቀው፤ "ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023” በሚል መሪ ቃል ከዛሬ ጀምሮ በአዲስ አበባ ስካይ ላይት ሆቴል የሚካሄደው የኢንቨስትመንት ፎረም ኢትዮጵያ ያላትን የኢንቨስትመንት አማራጭ በሚገባ ለማስተዋወቅ የሚረዳ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023 የተሰኘ የኢንቨስትመንት ፎረም መጀመሩን በማስታወቅ ከዓለም ዙሪያ ያሉ ባለሀብቶችን፣ የቢዝነስ መሪዎችን፣ ፖሊሲ አውጪዎችንና ስራ ፈጣሪዎችን በማሰባሰብ በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚያስተዋወቅ መሆኑን በመግለጫው ተጠቅሷል።

መግለጫው እንደሚያትተው፤ በፎረሙ ከ600 በላይ አዳዲስ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስተሮች የሚሳተፉበት ሲሆን፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያ ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያስችል አቅም ይኖረዋል።

ፎረሙ ክልሎች ያሏቸውን ሰፊ የኢንቨስትመንት አመራጮችን የሚያሳዩበት መድረክ ሲሆን፤ ለፎረሙ ተሳታፊዎች ስለ ኢትዮጵያ የቢዝነስ ሁኔታ፣ የኢንቨስትመንት እድሎች፣ የመንግስት ፖሊሲዎች ኢንቨስትመንትንና ኢኮኖሚን ለማሳደግ ስላላቸው ሚና እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

ከፎረሙ በቀጥታ በአጭር ጊዜ ውስጥ 500 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመነሻ ስምምነቶች ይኖራሉ። ከወሳኝ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ከ10 በላይ የመግባቢያ ስምምነቶች እንደሚኖሩም መግለጫው አስታውቋል፡፡

ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023 በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋ ሰጪ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚያሳይ ነው ያለው መግለጫው፤ በተለይ በማኑፋክቸሪንግ፣ ግብርና፣ ኢነርጂ፣ አይሲቲ፣ ጤና አጠባበቅ፣ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ፣ ቱሪዝምና ሌሎች ታዳጊ ዘርፎች ላይ ያተኮረ ነው።

ፎረሙ ባለሀብቶች ከሀገር ውስጥ ስራ ፈጣሪዎችና የመንግስት ባለስልጣናት ጋር እንዲገናኙ፣ አሁን ስላለው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ማበረታቻና ፖሊሲዎች እንዲያውቁ የሚረዳ ሲሆን፤ ከኢትዮጵያ የቢዝነስ አካላት ጋር የአጋርነት እድሎችን ለመዳሰስ እንደሚያስችልም ይጠበቃል፡፡



# ፍርድ ቤቱ በሽብር ወንጀል በተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ የ14 ቀናት የምርመራ ጊዜ ፈቀደ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ አንደኛ የጊዜ ወንጀል ችሎት ዶክተር ወንድወሰን አሰፋ፣ ዶክተር መሠረት ቀለመወርቅ እና ገነት አስማማው የተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ፖሊስ ያቀረበውን የ14 ቀናት የምርመራ ጊዜ ፈቅዷል፡፡

መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የፌዴራል ሥርዓቱን ኢ- ህገ መንግስታዊ በሆነ አግባብ በኃይል እርምጃ ለመቀየር በማቀድ ባዘጋጁት ስትራቴጂካዊ ሰነድ በመመራት በወታደራዊ ሥልጠና ክንፍ የፖለቲካ ክንፍ፣ በሚዲያ ፕሮፖጋንዳ ክንፍ እና ሌሎች የድርጊት መርሃ ግብር አፈጻጸምን በማውጣት መዋቅራቸውን በመዘርጋት፤ የሥራ ስምሪትና ክፍፍል በማድረግ፤ በህቡዕ ገንዘብ በማሰባሰብና በመመደብ፤ ታጣቂ ኃይል በማሰልጠንና በማደራጀት፤ በማስታጠቅ እንዲሁም በትጥቅ የታገዘ ህዝባዊ አመፅን በመቀስቀስ፤ የሥራ ማቆም አድማን በመቀስቀስ እንዲሁም የፋይናንስ ገቢ ለማግኘት ህገወጥ የፋይናንስ ሰንሰለትን እስከ ውጪ ድረስ በመዘርጋት ለሽብር ተግባር ገቢ ሲያሰባስቡና ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በተቀናጀ መልኩ ለሽብር ስራ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ናቸው ብሎ መጠርጠሩን የምርመራ መነሻ ለፍርድ ቤቱ አቅርቧል፡፡

ተጠርጣሪዎች ዓላማቸውን ለማሳካት እንዲያመቻቸው በማቀድ ተቻችሎና ተፋቅሮ የሚኖረው ህብረተሰብ መካከል እርስ በርስ መጠላላትንና መጠራጠርን በመንዛትና በመቀስቀስ አንዱን ህዝብ በሌላ ህዝብ ላይ እንዲነሳ በተደራጀ መልኩ ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል ሲል መርማሪ ፖሊስ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አስረድቷል፡፡

በዚህ ህገ ወጥ እንቅስቃሴያቸው ምክንያት የበርካታ ዜጎች ህይወት እንዲቀጠፍ፣ የህዝብና የመንግስት ንብረቶች እንዲወድሙ፣ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲቋረጥ፣ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንዲቆምና በየጊዜው እንዲስተጓጎል፣ የሥራ ማቆም አድማ እንዲደረግ አመጽን በመቀስቀስ የሽብር ድርጊት ወንጀልን በመፈጸም በንጹሐን ዜጎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ሲል መርማሪ ፖሊስ ለፍርድ ቤቱ አስረድቷል፡፡ ለዚህም 14 የምርመራ ቀናት እንዲሰጠው ጠይቋል።

የተጠርጣሪ ጠበቆች በበኩላቸው መርማሪ ፖሊስ ያቀረበው አቤቱታ ሊያስጠረጥር የሚችል የወንጀል መነሻ የለውም በማለት የምርመራ ቀጠሮ ውድቅ ተደርጐ የተጠርጣሪዎቹ የዋስትና መብት እንዲከበር ተከራክረዋል።

ተጠርጣሪዎቹ የተጠረጠሩበት የሽብር ወንጀል ድርጊት ውስብስብ እና የሀገርን አንድነት የሚያፈርስ፣ በህዝብ መካከል መተማመን እንዳይኖር፣ ዜጎች በሠላም ወጥተው እንዳይገቡ፣ በአገሪቱ ሥርዓት አልበኝነት እንዲሰፍን ለማድረግ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ለሽብር ተግባር ሲንቀሳቀሱ የነበሩና በርካታ ሥውር የአገር ማፍረስ ሴራዎች ያሉበት ነው ብሎ ፖሊስ ተከራክሯል።

ተጠርጣሪዎቹ በዋስ ቢወጡ ከአገር ሊሸሹና ሌሎች ማስረጃዎችንም በማሸሽ ምርመራውን ሊያደናቅፉ የሚችሉ መሆናቸው ታምኖበት የምርመራ ስራውን በስፋት በሰውና በሰነድ ማስረጃ አጣርቶ ለሚመለከተው የፍትህ አካል ማቅረብ እንዲቻል የ14 ቀን የምርመራ ማጣሪያ የጊዜ ቀጥሮ እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡

ክርክሩን የተከታተለው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት የተጠርጣሪዎቹን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ አድርጐ መርማሪ ፖሊስ የጠየቀውን 14 ቀናት የምርመራ ማጣሪያ የጊዜ ቀጠሮ ፈቅዷል፡፡


አቶ መላኩ አለበል

# በዘጠኝ ወራት የሁለት ቢሊዮን ዶላር ተኪ ምርቶች በአገር ውስጥ ተመርተዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት የሁለት ቢሊዮን ዶላር ተኪ ምርቶች በአገር ውስጥ መመረታቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። በተመሳሳይ ወራት ውስጥ ከእንጀራ ኤክስፖርት 28 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱም ተነግሯል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ በትናንትናው ዕለት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያና ምላሽ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ተኪ ምርቶችን ማምረት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ ቆይቷል።

በዚህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት የሁለት ቢሊዮን ዶላር ተኪ ምርቶች በአገር ውስጥ መመረታቸውን አስታውቀዋል፡፡

በተለይ የአግሮ ኢንዱስትሪ እና ምግብ እና ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች ላይ በተሠራው ሥራ አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ እነዚህን ምርቶች ለመተካት በተደረገ ጥረት አንድ ነጥብ 15 ቢሊዮን ዶላር ተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ መመረታቸውን አብራርተዋል። ይህንን ውጤት በመጪዎቹ ወራት ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ብቅልን የመሳሰሉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ከመተካት ባለፈ ኤክስፖርት ማድረግ መጀመሩን የጠቀሱት አቶ መላኩ፤ እንጀራን ከመሳሰሉ እሴት የታከለባቸው ምርቶች ከፍተኛ ገቢ እየተገኘ ነው ብለዋል። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ ከእንጀራ ኤክስፖርት 28 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘት መቻሉንም ጠቅሰዋል።

እንጀራ ኤክስፖርት የሚደረገው በጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ በተደራጁ አምራቾች ደረጃ ወጥቶለት መሆኑን የጠቀሱት አቶ መላኩ፤ ከእንጀራ ኤክስፖርት የተገኘውን ገቢ ጤፍን ብንልክ ልናገኘው አንችልም ብለዋል፡፡ ቡና እና ሌሎች ምርቶችንም በተመሳሳይ መንገድ ጥራታቸውን ጠብቀው እና እሴት ተጨምሮባቸው እንዲሸጡ ማስቻል አለብን ሲሉም አክለዋል፡፡

ምርቶች እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ መቅረብ እንዳለባቸው በመጠቆም፤ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የ120 ሚሊዮን ሕዝቦች ሀገር ስለሆነች ሁሉንም ነገር ከውጭ በሚመጣ ምርት ጥገኛ ሆኖ መቀጠል አስፈላጊ አይደለም ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ መንጠልጠል ሀገርን ሊያሳድግ የማይችል በመሆኑ በሀገር ውስጥ የምናመርትበትን እና የምንተካበትን ሁኔታ ከዚህ የበለጠ ማሳደግ ይኖርብናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ባለፉት ዘጠኝ ወራት አበረታች ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ባለፉት ዘጠኝ ወራት 67 የሚደርሱ አዳዲስ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡

# የአማራ ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የክልሉ የመንግስት አካላት ከሱዳን ወደ ክልሉ እየገቡ ያሉ ተፈናቃዮችን እየተቀበሉ መሆናቸውን ጠቁመው፤ የአካባቢው ማህበረሰብ ለተፈናቃዮች ምግብና የመጠጥ ውሃ እያቀረበ ነው ብለዋል፡፡

በሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት ወደ አማራ ክልል የገቡና እየገቡ ያሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች አካባቢው ተረጋግቶ ወደ ቀያቸው እስኪመለሱ ድረስ ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ እንዳይሆኑ የክልሉ መንግስት ከፌዴራል መንግስት ጋር በቅንጅት በመስራት ሰብአዊና ቁሳዊ ድጋፍ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የክልሉ አመራሮች ያለውን ችግር በመረዳት በሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት የተፈናቁሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎችን ለመርዳት ውይይት ማድረጋቸውን አቶ ግዛቸው ጠቁመው፤ ወደ ክልሉ የገቡና እየገቡ ያሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎችን በመቀበል የፌዴራል መንግስት የተለያየ ድጋፍ እስኪያቀርብላቸው ድረስ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል የክልሉ መንግስት ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

የክልሉ መንግስት ከፌዴራል መንግስት ጋር በመተባበር ወደ ክልሉ ለገቡና እየገቡ ላሉ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ወደ ፊትም አስፈላጊውን የሰብአዊና ቁሳዊ እርዳታ ለማቅረብ እንደሚሰራ አቶ ግዛቸው አመላክተዋል፡፡

# “የኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአገር ሉዓላዊነትን በሚፈታተኑ ጦርነቶች ድል በመቀዳጀት ከፍተኛ ድርሻ መጫወቱን አስታውሰው ፤ በተለያዩ ዘመቻዎች መሳተፉንና አኩሪ ድል እንዲመዘገብ የበኩሉን ድርሻ መጫወቱን ጠቅሰዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ይህ አንጋፋ ተቋም ኢትዮጵያን የሚመጥን የሪፎርም ሥራዎች ሲያካሂድ መቆየቱን ተናግረዋል። በተለይ በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ራሱን በማደራጀትና ዘመን የወለዳቸውን ትጥቆችና ተዋጊ አውሮፕላኖች እያሟላ ይገኛልም ብለዋል።

ተቋሙ ባለፉት አራት አመታት በተለይ በጥገና ዘርፍ ባከናወናቸው የሪፎርም ስራዎች ቀደም ሲል በውጭ ሀገር ሲካሄዱ የነበሩ የጥገና ስራዎችን በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች የማከናወን ብቃት መፍጠሩ የለውጡ አንዱ ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላምን ለማጽናት የተደረገ ቁርጠኛ ውሳኔ !

የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት ዓመታት በተለይ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ሲካሄድ የቆየው ጦርነት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ያሳየው ጽኑ አቋም በጽኑ አቋሙ መሰረት ተፈጽሟል፡፡ ጦርነቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ዓለም አቀፉ ማኀበረሰብና የተለያዩ ሀገሮች ጥያቄዎችን ሲያቀርቡም፣ ችግሩ አፍሪካዊ ነው፤ መፍትሄውም አፍሪካዊ መሆን አለበት የሚል ጽኑ አቋም አራምዷል፡፡ እንዳለውም መፍትሄው በአፍሪካ ልጆች እውን ሆኗል፡፡

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ መንግስትና ሕወሓት ባደረጉት ስምምነት ጦርነቱ ቆሟል፤ በአንዳንድ ሀገሮች እንደሚደረገው በስምምነቱ ጦርነቱ ብቻ አይደለም የቆመው፡፡ በስምምነቱ መሰረት የተቀመጡ ሌሎች አንኳር ጉዳዮችም እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡፡

መንግስት ለሰላም ስምምነቱ ባለው ቁርጠኝነት ለሰብአዊ አገልግሎቶች የሚውሉ የምግብ፣ የመድኃኒትና የመሳሰሉት አቅርቦቶች በሁሉም አማራጮች ሳይውል ሳይድር ነው የተጀመሩት፡፡ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ብዙም ሳይቆይ ወዲያው ተጀምሯል፤ በጦርነቱ የተጎዱ መሰረተ ልማቶች እየተጠገኑ ወደ ስራ ተመልሰዋል፤ አገልግሎት አቁመው የነበሩ በርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስራቸውን ጀምረዋል። ሕወሓትም ከባድ መሳሪያዎቹን አስረክቧል፤ በትግራይ የሽግግር አስተዳደር ተመስርቷል፡፡ የትምህርትና የመሳሰሉት ተቋማት እንዲከፈቱ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው፡፡

የአውሮፕላን በረራ መጀመሩን ተከትሎ በጦርነቱ ሳቢያ ተለያይተው የነበሩ ቤተሰቦች መገናኘት ከጀመሩ ቆይተዋል፤ በቅርቡም የሀገር አቋራጭ አገልግሎት በአፋር በኩል ተጀምሯል። ተመሳሳይ አገልግሎት በአማራ ክልልም በኩል እንዲጀመር በጊዜያዊ አስተዳደሩ እየተጠየቀ ነው፡፡ በቅርቡም የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በትግራይ ክልል ጉብኝት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፤ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደርም እንዲሁ በሌሎች ክልሎች ጉብኝት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡

ከዚህ ሁሉ መረዳት እንደሚቻለው በሰሜን ኢትዮጵያ የሰላም አየር እንዲነፍስ የማድረጉ ስራ በተያዘለት አቅጣጫ መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን ነው፡፡ ሁሉም ወገኖች ሰላሙን ለማጽናት ርብርብ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ለሰላም ከዚህም በላይ ርብርብ ማድረግ እንዳለባቸው እየተገለጸ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለሰላም ስምምነቱ ለሰሩ እውቅና በተሰጠበት ስነስርአት ለሰላም እንዲጀገን ባሳሰቡት መሰረት ሰላሙን ለማጽናት ርብርቡ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

በሀገሪቱ ባለፉት አመታት የተፈጠረው የሰላም እጦት የስፋት፣ የጥበት፣ የጥልቀት ልዩነት ያለው ካልሆነ በቀር በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም ፀጥታ የደፈረሰበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ በየትኛውም ስፍራ ለሚታየው የጸጥታ መደፍረስ ተጠያቂ የሆኑ አካላትን በህግ አግባብ መጠየቅ አንድ ነገር ሆኖ ለሰላም የሚጨምረው ነገር አለ ተብሎ እስከ ታመነበት ድረስ ከእነዚህ አካላት ጋር መነጋገርና ለሰላም ቅድሚያ መስጠት ብልህነት ስለመሆኑ ከሕወሓት የተደረሰው ስምምነትና በስምምነቱ መሰረት እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮች ያመለክታሉ።

እንደሚታወቀው መንግስት በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ ዞኖች እየተንቀሳቀሰ ጥቃት የሚሰነዝረውን ሸኔ ለመቆጣጠር የሀገሪቱ የጸጥታ ኃይሎች ርምጃዎችን ሲወስዱ ቆይተዋል፤ አሁንም እየወሰዱ ነው፡ ይህ ከሸኔ ጋር ሲደረግ የነበረው ግጭት ኀብረተሰብን እየጎዳ ብዙ ጊዜያትን መውሰዱ ይታወቃል፡፡

ቡድኑ በንጹኃን፣ በመሰረተ ልማትና በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ማኀበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ጥቃት አድርሷል። በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች የሰዎች እንቅስቃሴና ሕይወት ስጋት ውስጥ ወድቆ ቆይቷል፡፡ በተለይ በወለጋ አካባቢ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች በአግባቡ እንዳይካሄዱ አድርጓል፡፡

መንግስት ከዚህ ቡድን ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ መያዙን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይፋ አድርገዋል። ይህ የመንግስት ውሳኔ አሁንም ለሰላም የተከፈለ ትልቅ ዋጋ ነው፡፡ መንግስት ከሕወሓት ጋር እንደተወያየና ለሰላም ስምምነት እንደደረሰ ሁሉ ከዚህ ቡድን ጋርም ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ ለዘላቂ ሰላም ለምን አይሰራም ሲሉ ለቆዩ ወገኖችም ምላሽ ይሆናል፡፡

ቡድኑ በአሸባሪነት የተፈረጀ ፣ በዜጎች ህይወት፣ ሀብትና ንብረት፤ በመንግስት ሀብትና ንብረት፣ በሀገር ሰላምና ጸጥታ ላይ ብዙ ጉዳት ያስከተለ፣ አሁንም ስጋት ሆኖ የቀጠለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ መንግስት ለእዚህ ውሳኔ የደረሰው አሁንም ለዘላቂ ሰላም ሲል መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ቡድኑ ያደረሰው ጥፋት በእጅጉ የሚያም ቢሆንም፣ ለዘላቂ ሰላም ከበጀ መወያየትም ትልቅ እርምጃ ተደርጎ ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ የመንግስት ውሳኔ ተገቢነት ያለውና በሀገሪቱ ሰላምን ለማጽናት የያዘው ቁርጠኛ አቋም የታየበት በድጋሚ ነው፡፡

ይህ የመንግስት ውሳኔ መንግስት ለዘላቂ ሰላም ሲል ከሕወሓት ጋር ለመወያየት ባሳየው ቁርጠኛ አቋምና እሱን ተከትሎ በተደረሰው የሰላም ስምምነት የመጡ ለውጦች የሰላም መደፍረስ ባለባቸው የሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች እውን እንዲሆኑ ትልቅ አቅም በመሆን ያገለግላል፡፡

የሰላም ጎዶሎ የለውም፤ ሙሉ ነው፡፡ በአንድ አካባቢ ሰላም ሰፍኖ በሌላ አካባቢ ሰላም የሚደፈርስ ከሆነ ሀገር ዥንጉርጉር ትሆናለች፤ ከችግርም አይወጣም፡፡ ሰላሙ አንጻራዊ ቢሆን እንኳ በአንዱ አካባቢ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ተሰርቶ ሌላው ዘንድ አለመስራቱ የሰላም ማስፈኑን ስራ ያዥጎረጉረዋል፡፡ በመሆኑም በሰሜን ኢትዮጵያ እየታየ ያለው ሰላም በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎችም እንዲደገም ለማድረግ መስራት በየትኛውም መመዘኛ ትክክለኛ ውሳኔ ነው፡፡

እንደሚታወቀው በሰላም ውይይት በኩል የኢትዮጵያ መንግስት የቅርብ ጊዜ ተሞክሮ አለው፡፡ ይህን ተሞክሮ ከሸኔ ጋር በሚደረገው ውይይትም በመተግበር በሀገሪቱ ዘላቂና ሙሉ ሰላም ለማምጣት የተጀመረው ጥረት ውጤታማ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡ በሸኔ በኩል የሚደራደሩ ወገኖችም እንዲሁ ሰላምን ለማጽናት ለሚያስችሉ ሀሳቦች ቅድሚያ በመስጠትና ከልብ በሆነ የሰላም ፍላጎት ለውይይቱ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70




## “ዓውዳችን ሰላም፤ ቋንቋችን ልማት እና አብሮነት መሆን ይኖርበታል”

*- አቶ ደመቀ መኮንን፣*
*ም/ጠ/ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር*

**ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ “ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና“ በሚል መሪ ሀሳብ በተካሄደው ሰላም የማፅናት የዕውቅና መርሐ ግብር ላይ ያደረጉት ንግግር**

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ “ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና” በሚል መሪ ሀሳብ በተካሄደው ሰላም የማፅናት የዕውቅና መርሐ ግብር ላይ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል። መልዕክታቸውም “ሃገራችን ፋታ ትፈልጋለች፤ ሕዝባችንም ሰላም እና ደህንነቱ እንዲጠበቅ እና ሕይወቱ ወደተቃና አቅጣጫ እንዲመለስለት ይጠብቃል፤ ለዚህም ዓውዳችን ሰላም፣ ቋንቋችን ልማት እና አብሮነት መሆን ይኖርበታል፤” ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንንን ሙሉ ንግግር እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ክቡራን አፈጉባኤዎች፣ ክቡር ሙሳ ፋኪ ማሃማት የአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ኮሚሽን ሊቀመንበር፣ ክቡራን የቀድሞ ፕሬዚዳንቶች፣ ክቡራን የኅብረቱ የፓናል አባላት፣ ክቡራን የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ክቡራን ሚኒስትሮች፣ ክቡር የኢጋድ ዋና ፀሐፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ፣ ክቡራን የዕለቱ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣ ክቡራት እና ክቡራን፤

በቅድሚያ ሁሉን አውዳሚ የሆነው ጦርነት ቆሞ በተጀመረው ሰላም የማፅናት እና የዕውቅና ፕሮግራም ላይ ለመታደም ስለበቃን በሰላም ኮሚቴው እና በራሴ ስም እንኳን አደረሳችሁ! እንኳ አደረሰን ለማለት እወዳለሁ፡፡

ከአውዳሚው ጦርነት በመውጣት ወደ ሰላም ለመምጣት በኢትዮጵያ ባለቤትነት፣ በአፍሪካ ኅብረት መሪነት በተለይም “ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ” በሚለው መርሕ መሠረት የሠላም ስምምነት ተደርሷል። ሂደቱም በመልካም አፈፃፀም ላይ ይገኛል፡፡ ለእዚህ ስኬት የበኩላችሁን ወሳኝ አስተዋፅኦ ለተጫወታችሁ እና ድጋፍ ላደረጋችሁ ሁሉ ምስጋናችን የላቀ ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት በነበረው የተሳሳተ ብሒል ማለትም እኔ ያልኩት ካልሆነ እልህና ራስን ብቻ የማዳመጥ የፖለቲካ ትርክት፤ ምን ያህል የከፋ ደረጃ ላይ አድርሶን እንደነበረ፤ አሁን የተፈጠረውን ሠላም ተጠቅመን በተረጋጋ መንፈስ ራሳችንን በመጠየቅ ሥልጡን ፖለቲካን ያልተከተለ እና ዘመኑን ያልዋጀ ጉዞ መዳረሻ ውጤቱ ከፍተኛ ውድመት እና አሳዛኝ ጥፋት መሆኑን ከታሪክ ሳይሆን ከተግባር ተምረናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

የዛሬው መርሐ ግብር ከመጣንበት ስሁት መንገድ በፍጥነት ወጥተን፤ አዲስ ሁሉን አካታች የመደጋገፍ የረጅም ጉዞ እርካብ ለመጨበጥ እንድንችል እና በመንገዳችን ላይ ለሚያጋጥሙን የፖለቲካ ስብራቶች ሀገራዊ መፍትሔ እየሰጠን የሰላም ሂደቱን ለማጽናት እንዲቻል በሂደቱ የተሳተፉትን ሁሉ ለማመስገን፤ አክብሮታችንን ለመግለጽ የተዘጋጀ የምስጋና ፕሮግራም ነው፡፡

እንደሚታወቀው ባለፉት ሁለት ዓመታት ያለፍንበት የጦርነት ወቅት በሃገራችን እና በሕዝባችን ላይ ዘርፈ ብዙ ጉዳት አስከትሏል፡፡ መተኪያ የሌለውን የባርካታ ዜጎቻችንን ሕይወት ቀጥፏል፡፡ ግጭቱ ከፍተኛ የሆነ የሥነ ልቦና ጉዳት አድርሷል፡፡ ሃገራችን በግጭቱ፤ በጦርነቱ ምክንያት በተሟላ ሁኔታ ለመገመት አዳጋች የሆነ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊ የመሠረተ ልማት እና ሌሎች ከባድ ውድመት ደርሶባታል፡፡ ግጭቱ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ተስፋ ነጥቋል፡፡ ወጣቶቻችን ነገን ለበጎ ሲያቅዱ እሩቅ አላሚ የቅርብ አዳሪ አድርጓቸዋል። ባጭሩ ላልተበደሩት እዳ ከፋይ ሆነዋል፡፡


በተስፋ የያዝነው ሰላም ሂደት ከግቡ እንዲደርስ ስምምነት የተደረሰባቸውን ነጥቦች ያላንዳች ማመንታት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ሃገራችን ፋታ ትፈልጋለች፡፡ ሕዝባችን ሰላም እና ደህንነቱ እንዲጠበቅ እና ሕይወቱ ወደተቃና አቅጣጫ እንዲመለስለት ይጠብቃል፡፡ ዓውዳችን ሰላም፤ ቋንቋችን ልማት እና አብሮነት መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ እውን እንዲሆን በሁሉም ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል፡፡ ሕዝብ የሚያነሳቸውን ጥቄዎች ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዘላቂ መፍትሔ በሚያስገኝ አግባብ መፍታት ይኖርብናል። የግንኙነት አግባብነታችን እና የዕለት ግንኙነታችን ሕዝቡን የሚያቀራርብ እና ሰላምን የሚያጸና መሆን አለበት፡፡

ከአሉባልታ እና ስሜታዊነት በመራቅ ሁሉንም ወገን እና ባለድርሻ ያማከለ፤ ከሁሉም በላይ ሃገርን ማዕከል ያደረገ እና የሕዝብን ትክክለኛ ስሜት የተጋራ መሆን አለበት፡፡ የተወሰኑ ቡድኖችን እና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማስደሰት፤ ድጋፍ ለማድረግ የሚደረጉ ነጣይ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ዘላቂነት አይኖራቸውም፡፡ የሁሉንም ድምጽ አዳምጠን፤ በየልኩ እውቅና ሰጥተን፤ የሚጎድለውን ሞልተን፤ የሕዝቦቻችንን ሃገር በቀል የመፍትሔ መንገዶችን በማጠናከር ሃገራዊ የምክክር ሥራችንን አጎልብተን፤ የሽግግር ፍትሕ እንቅስቃሴው መንገዶችን በማጠናከር ሃገራዊ የምክክር ሥራችንን አጎልብተን የሽግግር ፍትሕ እንቅስቃሴውን አጠናክረን የገጠመንን ታሪካዊ ችግር በታሪካዊ እሴት መወጣት ይገባናል፡፡ በግጭት የተነሳነው ስማችን አድሰን ከጎናችን ለቆሙት አፍሪካውያን እንዲሁም ለቀረው ዓለም አስተማሪ በሚሆን መንገድ የተስማማንበትን መፈጸም ይገባናል፡፡ ይህንን እንደምናሳካ ጥርጥር የለኝም፡፡ እንችላለንም! አመሰግናለሁ፡፡

# ፍረዱኝ

# «አባቴ ለመንግሥት በአደራ የሰጠውን ቤት ለመውሰድ ተከልክያለሁ»

- አቶ ጌታቸው ከበደ
አቤቱታ አቅራቢ


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
በኮ/ቤ/ል/ጽ/ቤት የቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ

AKAKI KALITY SUB CITY ADMINISTRATION DESIGN CONSTRUCTION ADMINISTRATION AND DEVELOPMENT OFFICE
HOUSING DEVELOPMENT ADMINISTRATION SUB PROCESS

ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ቤ/ል/አስ/የሥ/ሃ/ /04
ቀን 16/12/2004 ዓ.ም.

በኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ
- ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በማካካሻ ስለተሰጠ ቤት ውሳኔ ስለመጠየቅ፤

አቶ ጌታቸው ከበደ አባታቸው አቶ ከበደ ወንድምጊዜ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የሚገኘውን የግል ቤታቸውን በማካካሻ ለወረዳው ያስረከቡትን ቤት ተመልሶልኝ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 7 /የቀድሞ ቀበሌ 08/16/ የቤት ቁጥር 077 የሆነውን ቤት ተረከቡኝ በማለት ጠይቀዋል፤

በዚሁ መሠረት መረጃዎችን በምናጣራበት ወቅት ከአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ምንም አይነት መረጃ ማግኘት ያልተቻለ ሲሆን ግለሰቡ በእጃቸው ከያዙትና የጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ኮ/ቤ/ል/ጽ/ቤት ከላከልን የተወሰነ መረጃ ማግኘት ተችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት ግለሰቡ በማካካሻነት ያስረከቡበትና የተረከቡበት ማስረጃዎች ኮፒ እና ቅፅ 003-ከ1-8፣ ቅፅ 007 1 እና 2 ቤት ያስረከቡበትና ቤቱ የሚገኝበት ሁኔታን የሚገልፅ ማስረጃ ኮፒዎች ቀርበዋል፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ያስረከቡትን ቤት ያለበትን ሁኔታ ስናይ በ1967-68 ዓ.ም የቤት ቁጥር የሌለው ሲሆን በወቅቱ ከግለሰቡ የተከራዩ 3 ግለሰቦች አሁን የቤት ቁጥር 395፣396፣397 ተሰጥቷቸው ቤቶቹ ኪራይ እየተከፈለባቸው ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም የግለሰቡ ጥያቄ የቤት ቁጥር 195፣196፣197 አንድ ቤት የነበሩ ስለሆነ ይመለስልኝ የሚል ሲሆን በክ/ከተማችን በኩል ግን የትኛው ቤት በምን አግባብ ሊመለስ እንደሚችል የተቸገርን ሲሆን በኤጀንሲው በኩል ምላሽ እንዲሰጥ እየጠየቅን ያሉትን መረጃዎች ኮፒ--------ገፅ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ
- ለኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት
- ለወረዳ 03 ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት
-

አዲስ አበባ

011 439 15 15 መልስ ሲጽፉ የእኛን ቁጥር ይጥቀሱ፡፡ ፋክስ 011 439 10 25

ሙሉቀን ታደገ

ክፍል አንድ

**የዛሬው የፍረዱኝ አምድ ዝግጅታችን የጉለሌ እና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞችን እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት አስተዳደርን መዳረሻው ያደረገ ነው።**

**«በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኘውንና በ1968 ዓ.ም ወላጅ አባቴ ለመንግሥት በአደራ የሰጠውን ቤት አሁን ላይ እንዲመለስልኝ ብጠይቅም የጉለሌ እና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት አስተዳደር በአደራ የወሰዱትን ቤት ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ስለሆነም በቤቶች አስተዳደር የተፈጸመብኝን በደል የኢትዮጵያ ሕዝብ አይቶ ይፍረደኝ» ሲሉ አቶ ጌታቸው ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል።**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ግራ እና ቀኙን አይቶ መፍረድ ይችል ዘንድ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን ማስረጃዎች መርምሮ እንደሚከተለው አቅርቧል፤ መልካም ንባብ።**

### አቤቱታ አቅራቢው

አቶ ጌታቸው ከበደ ወንድምጊዜ ይባላሉ። ነዋሪነታቸው በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ ነው። ከ2007 ዓ.ም በፊት በተለምዶ አዲሱ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት የቤት ቁጥር 077 ይኖሩ ነበር።

አቤቱታ አቅራቢው እንደሚናገሩት፤ አባታቸው አቶ ከበደ ወንድምጊዜ የኮሪያ ዘማች ነበሩ። ከኮሪያ ዘመቻ መልስ በቀድሞ ስሙ አቃቂ ከተማ አንደኛ ጩሎ ቀበሌ በአሁኑ መጠሪያው ደግሞ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ ሦስት አካባቢ የቴሌኮሙኒኬሽን ሠራተኛ በመሆን ተቀጠሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ለሥራ ቦታቸው ቅርብ አካባቢ በመፈለግ በ1953 ዓ.ም አበበች አባደፋር ከተባሉ ወይዘሮ በ200 ብር 144 ካሬ ሜትር ቦታ ገዙ። ከ1953 ዓ.ም እስከ 1967 ዓ.ም በቦታው መኖር ቻሉ። በ1967 ዓ.ም በአቃቂ ከተማ ጩሎ ቀበሌ ከሚሠሩበት መስሪያ ቤት ወደ ሱልልታ ሳተላይት እንዲዘዋወሩ ተደረገ። ይህ አጋጣሚ በአቶ ጌታቸው እና ቤተሰባቸው ሕይወት ላይ ሁሉን ቀያሪ ክስተት እንዲፈጠር አደረገ።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ በመንግሥት በተደረገው ምደባ የአባታቸው የአቶ ከበደ ወንድምጊዜ የሥራ ሁኔታ ከአቃቂ ወደ ሱሉልታ ሳተላይት በአዘዋወረበት ወቅት እንደ አሁኑ በቀላሉ የትራንስፖርት አገልግሎት አይቻልም ነበር። በዚህም ምክንያት አቶ ከበደ በቃሊቲ የሚገኘውን ቤታቸውን በማከራየት በተለምዶ አዲሱ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተከራይተው እንዲኖሩ ይገደዳሉ።

አዲሱ ገበያ አካባቢ ቤት ተከራይተው እየኖሩ እያለ፤ በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ይመጣል። የደርግ ወታደራዊ መንግሥት በትረ መንግሥቱን ይቆጣጠራል። የደርግ መንግሥት ወደ ስልጣን መምጣቱን ተከትሎ 47/67 አዋጅ ታወጀ። በዚህ አዋጅ ትርፍ ቤት ያላቸው ሰዎች እንዲወረሱ ተደረገ። ከዚህም ባሻገር በአዋጁ በተለያዩ ምክንያቶች ዜጎች ይኖሩበት የነበረውን ቤታቸውን ለቀው ወደ ሌላ ቦታ የሚሄዱ ከሆነ ቤታቸውን በአደራ ለመንግሥት መስጠት እንደሚችሉ እና በአደራ በሰጡት ቤት ልክ ደግሞ በሄዱበት አካባቢ መንግሥት በማካካሻነት በነፃ ቤት መስጠት እንደሚገባው በአዋጁ ተደንግጓል።

ይህን አዋጅ የሰሙት አቶ ከበደ ወንድምጊዜ የተባሉ ግለሰብ በሥራ ምክንያት በቀድሞው ስሙ የአቃቂ ከተማ አንደኛ ጩሎ ቀበሌ በአሁኑ መጠሪያው አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የሚገኘውን ቤታቸውን ለመንግሥት በ47/67 አዋጅ መሠረት በማስረከብ ለሥራቸው ቅርብ የሆነ የማካካሻ ቤት እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። ይህን ጥያቄ ተከትሎ የአቃቂ ከተማ የአንደኛ ጩሎ ቀበሌ በቁጥር 1172777 250 ፅኑ በኅዳር 9 ቀን 1968 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለጉለሌ ወረዳ ቀበሌ በቀድሞ መጠሪያው 01/01/04 የህብረት ሥራ ማህበር ጽሕፈት ቤት፤ በአሁኑ መጠሪው ደግሞ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ደብዳቤ መላካቸውን ሰነዶች ያመላከታሉ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በቁጥር 4949/ጉ/68 መስከረም 26 ቀን 1968 ዓ.ም ለ10/01/04 የህብረት ሥራ ቀበሌ በተጻፈ ደብዳቤ በቃሊቲ የሚገኘው የአቶ ከበደ ወንድምጊዜ ቤት በ20 ብር እየተከራየ ይገኝ እንደነበረ እና አሁን ላይ በአዋጅ 47/67 ለአዲስ አበባ ማዘጋጃ ያስረከቡ ስለሆነ በጉለሌ ወረዳ የሚኖሩበትን ቤት የሕጉ መንፈስ በሚያዝዘው መሠረት ከኪራይ እንዲድኑ ስለጠየቁ አስፈላጊው ትብብር ይደረግላቸው የሚል ደብዳቤ ለጉለሌ ወረዳ ላከ።

ይህን ተከትሎ በጉለሌ ወረዳ በቀድሞ ስሙ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር 077 በአሁኑ መጠሪያው ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ከኪራይ ነፃ የሆነ ቤት በ1968 ዓ.ም እንዲያገኙ መደረጉን ሰነዶች ያሳያሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ሰነዶች እንደሚያሳዩት፤ የደርግ መንግሥት ወደ ስልጣን እስከመጣበት እና ቤቱን በአደራ ለመንግሥት እስካስረከቡበት ጊዜ ድረስ በአቃቂ ከተማ ይገኝ የነበረው ቤት በአቶ ከበደ ወንድምጊዜ ስር ይተዳደር ነበር።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ አባታቸው አቶ ከበደ ወንድምጊዜ በ1973 ዓ.ም ሕይወታቸው አለፈ። ነገር ግን አቶ ከበደ ወንድምጊዜ ሕይወታቸው ከማለፉ በፊት ቀደም ብሎ በ1968 ዓ.ም ለመንግሥት በአደራ የሰጡትን ቤታቸው እንዲመለስላቸው ለጉለሌ ወረዳ ጥያቄ አቅርበው ነበር። ነገር ግን የጠየቁት ጥያቄ ሳይመለስ እና ጥያቄያቸው በሂደት ላይ እያለ ሞት ቀደማቸው።

የዛሬው አቤቱታ አቅራቢ በወቅቱ ሕፃን ስለነበሩ የአባታቸውን ጥያቄ ለማስቀጠል ሳይችሉ ቀሩ። አባታቸው በሕይወት እያሉ ለጉለሌ ወረዳ ጠይቀውት የነበረውን የአደራ ቤት ይመለስልኝ ጥያቄ ሳያነሱ ከጉለሌ ወረዳ በማካካሻነት በተገኘው ቤት ከእናታቸው እና ወንድማቸው ጋር ለበርካታ ዓመታትም ቆዩ።

ቀን ቀንን ሲወልድ የዛሬው አቤቱታ አቅራቢው ለአቅመ አዳም ደረሱ። አባታቸው ከመሞታቸው በፊት አንስተውት የነበረውን የአደራ ቤቱ ይመለስልኝ ጥያቄ እርሳቸውም መልሰው ለማንሳት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ያሉ ባለሙያዎችን ማማከር ይጀምራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በ2004 ዓ.ም የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ሰነድ አልባ ቤቶች ሰነድ እንዲኖራቸው የሚያስችል መመሪያ አስተላለፈ የሚሉት አቶ ጌታቸው፣ ውሳኔውም ማስታወቂያው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም የመጨረሻ መጠናቀቅ እንዳለበት መመሪያ ተላልፎ እንደነበር ያስረዳሉ። ይህን ተከትሎ አቶ ጌታቸው ከበደ፣ 2004 ዓ.ም በመጋቢት ወር ላይ አባታቸው ለመንግሥት በአደራ የሰጡትን ቤት ለማስመለስ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ለወረዳ 07 የቤቶች ልማት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ ማስገባታቸውን ያስረዳሉ።

የአቤቱታ አቅራቢውን ማመልከቻ የተቀበሉት በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 07 ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ባለሙያዎችም ለአቤቱታ አቅራቢው አቶ ጌታቸው በአደራ ለመንግሥት የሰጡትን ወይም በማካካሻነት የወሰዱት ቤት አንዱን በመምረጥ ወደ ግል ይዞታ የመቀየር ሕጋዊ መብት እንዳላቸው እንደነገሯቸው ያስረዳሉ።

ይህን ተከትሎ አቶ ጌታቸው፣ በመመሪያው መሠረት በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በአደራ ለመንግሥት የተሰጠውን ቤታቸውን ለማስመለስ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ለወረዳ 07 ማመልከቻ በማቅረብ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ያብራራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ በ2004 ዓ.ም በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አመራሮች በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ከሚገኙ አመራሮች ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ይጀምራሉ። የመረጃ ልውውጡም ስድስት ወራትን እንደፈጀ የሚናገሩት አቶ ጌታቸው፣ ከመረጃ ልውውጡም በኋላ በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የሚገኘውን በአደራ ለመንግሥት ተሰጥቶ የነበረውን ቤት ይመለስለት ወደሚለው ውሳኔ መደረሱን ይናገራሉ።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ የአቃቂ ክፍለ ከተማ ቤቱን ለመመለስ ቢወስንም በመካከል ግን አንድ ችግር ተፈጠረ። ለተፈጠረው ችግር ዋናው ምክንያት ደግሞ መንግሥት በአቃቂ የሚገኘውን ቤት በ1968 ዓ.ም ከተረከበ በኋላ ኩሽና፣ መጸዳጃ እና እንዲሁም ከዋናው ቤት በተጨማሪ ያሉ ሌሎች በግቢው የነበሩ ክፍሎችን ለእያንዳንዳቸው የቤት ቁጥር ሰጥቷቸዋል። አባታቸው ለመንግሥት ቤቱን ሲያስረክቡ ግን ሁሉንም ቤቶች ያስረከቡት እንደ አንድ ቤት ነበር። አባታቸው በጉለሌ ወረዳ በማካካሻነት የተሰጣቸውን ሦስት ክፍል ቤትም የተረከቡት 077 በሚል አንድ የቤት ቁጥር ብቻ የተመዘገበ ቤትን ነበር። ነገር ግን መንግሥት በአደራ የተቀበለውን ቤት ለመጸዳጃውም፣ ለኩሽናውም፣ ለዋና ቤቱም የተለያዩ ቁጥሮችን ሰጥቷቸዋል።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በአደራ የተሰጡት ቤቶች የተለያዩ ቁጥሮች ቢሰጣቸውም እስካሁን ድረስ ቤቶቹ የጋራ መጸዳጃ እና ኩሽና ግን የላቸውም።

በአደራ ለመንግሥት የተሰጡ ቤቶች ለአቶ ጌታቸው እንዲመለሱ በአቃቂ ቃሊቲ እና በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ስምምነት ላይ ቢደረስም በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የሚገኘው የቤቶች አስተዳደር በአደራ የተረከበውን ቤት በተለያዩ ቁጥሮች እና ክፍሎች ከፋፍሎ ለተጠቃሚዎች ሰጥቶ ስለነበር ከእነኝህ ከተከፋፈሉ ቤቶች መካከል የትኛውን መመለስ እንዳለበት ስለተቸገረ ጉዳዩን ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ማሳወቁን ያስረዳሉ። በአደራ የተሰጠው ቤት የተለያዩ ቁጥሮች መሰጠታቸውን ተከትሎ ክፍለ ከተማውም እንደወረዳ 03 ጥያቄውን ለመመለስ ይቸገራል። ይህን ተከትሎ ክፍለ ከተማው ጉዳዩን ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ደብዳቤ ይፅፋል። የቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤትም አቶ ጌታቸው የማግኘት መብት እንዳለቸው ገልጾ ነገር ግን በወቅቱ በነበሩ መመሪያዎች በሙሉ ክፍተቶች አሉባቸው፤ ስለሆነም አሁን ባለው መመሪያ መሠረት የአቶ ጌታቸው ማመልከቻ ሊስተናገድ እንደማይችል ይገለፅላቸዋል።

በአደራ እና በማካካሻነት ከተያዙ ቤቶች ጋር በተያያዘ መመሪያው ክፍተት እንዳለበት የቤቶች ልማት ሥራ አስፈጻሚ ስለነገሯቸው እና ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት እንዲወስዱት አቅጣጫ ስለጠቆሟቸው በ2006 ዓ.ም ጉዳዩን ወደ አቃቂ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመውሰድ የአቃቂ ክፍለ ከተማን እና ወረዳ 03ን ይከሳሉ። ይሁን እንጂ በመዝገብ ቁጥር 3185/05 ሁለቱን ወገኖች ክርክር ሲያስተናግድ የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት «አቶ ጌታቸው ያነሱት ጥያቄ ተገቢነት የለውም» ሲል በ22/2/06 በዋለው ችሎት ብይን ሰጠ።

ይህን ተከትሎ አቶ ጌታቸው ይገባኝ ጠይቀው ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደወሰዱት የሰነድ ማስረጃዎች ያሳያሉ። በከፍተኛው ፍርድ ቤት

# ፍረዱኝ

በመዝገብ ቁጥር የኮመ/151114 በተከፈተ ፋይል ሁለቱን አካላት ሲያከራክር ከቆየ በኋላ በ1/8/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ ጌታቸው ያነሱትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ እና የስሩን ፍርድ ቤት ብይን አፅድቀናል የሚል መልስ በመስጠት ፋይሉ መዘጋቱም የሰነድ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይህን ተከትሎ መፍትሄ ያጡት አቶ ጌታቸው፣ ጉዳያቸውን በፖስታ በማደረግ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በመላክ «አቤት» ይላሉ። ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትም ለጉዳዩ አንዳንድ አቅጣጫዎችን ከማሳየት ባለፈ በቀጥታ እጃቸውን በጉዳዩ ውስጥ እንደማያስገቡ ጠቅሰው፤ ከአቃቂ ቃሊቲ ክፍከ ከተማ፣ ወረዳ 03 እና የአዲስ አበባ ቤቶች ውጪ ለሚገኙ ቅሬታ ሰሚዎች ጉዳዩን መውሰድ እንዳለባቸው አቅጣጫ እንደጠቆሟቸው ያስረዳሉ። ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትም በሰጣቸው አቅጣጫ መሠረት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ አቤቱታ ማስገባታቸውን ይናገራሉ።

የከንቲባ ጽሕፈት ቤት ቅሬታ ሰሚም ጉዳዩን ከተመለከቱ በኋላ ከአቃቂ ቃሊቲ እና ከጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ባለሙያዎችን ተፈጠረ ስለተባለው ችግር መረጃ እንዲልኩላቸው ጠየቁ።

ከሁለቱ ክፍለ ከተሞች ያሉ መረጃዎች በባለሙያዎች መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ መረጃዎች ወደ ቅሬታ ሰሚው አካል ተላከ። የተላከውን መረጃ መሠረት በማድረግ ቅሬታ ሰሚው አካል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሦስት የሚገኘው ቤት በመንግሥት በአደራ መልኩ ተይዞ የቆየው ቤት እንጂ በአዋጅ አለመወረሱን ፣ ምንም ዓይነት አበል እንደአልተበላበት በመጠቆም ለከንቲባ ቅሬታ ሰሚ ጻፉ።

ይሁን እንጂ ከቅሬታ ሰሚው የደረሰውን ደብዳቤ በፍርድ ቤት ታይቷል የሚል ምላሽ ሰጠ። ይህን ተከትሎ አቶ ጌታቸው ለቅሬታ ሰሚው ሁለተኛ ጊዜ በመሄድ ቅሬታቸውን አሰሙ። ነገር ግን ቅሬታ ሰሚው ከዚህ በላይ ስለጉዳዩ ማየት እንደማይችል ምላሽ እንደሰጣቸው ያስረዳሉ።


ተስፋ ያልቆረጡት አቶ ጌታቸው ጉዳዩን ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት ማስገባታቸውን ይናገራሉ። በወቅቱ ምክትል ከንቲባ የነበሩት አቶ አባተ ስጦታው፣ መረጃዎችን ከተመለከቱ በኋላ ጉዳዩን ለመሬት አስተዳደር መሩት። መሬት አስተዳደርም አቶ ጌታቸውን በመጥራት መረጃቸውን በማየት እና ስለጉዳዩ ጠርተው አነጋገሯቸው።


ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ መሬት አስተዳደርም ጉዳዩን ለባለሙያዎች መራው። እነዚያ ባለሙያዎች ጉዳዩን ከመረመሩት በኋላ ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ቢሮ በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሦስት ከቤት ቁጥር 395 እስከ 400 ያለውን መረጃ እና በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት የቤት ቁጥር 077 ያለውን የቤት መረጃዎች አጣርታችሁ ላኩልን ሲሉ አዘዙ። ነገር ግን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ቢሮ «ጉዳዩ የእኛ ጉዳይ ስለሆነ ለማዘጋጃ ቤቱ መረጃ የምንልክበት ምክንያት አይኖርም» ሲል መግለጹን አቶ ጌተቻው ያስረዳሉ።

ይህን ተከትሎ አቶ ጌታቸው በአካል ወደ አዲስ አባባ መሬት ልማት ቢሮ በመሄድ «ለምን የመሬት ማኔጅመንት የጠየቃችሁን መረጃ አትልኩም?» ሲሉ የመሬት ልማት አስተዳደርን መጠየቃቸውን ይገልጻሉ። የአዲስ አበባ መሬት ልማት አስተዳደርም ጉዳዩን በአግባቡ እንመረምርልሃለን እንዳሏቸው እና አቶ ጌተቻውም እነሱን በማመን ለበርካታ ጊዜያት በተስፋ እንደጠበቁ ያስረዳሉ።

ይህ በእዲህ እንዳለ፤ ጉዳዩን ለመመርመር ከሁለቱ ክፍለ ከተሞች እና ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቋመ። የተቋቋመው ኮሚቴም መረጃዎችን ሰብስቦ ሲያይ ቆየ ። ነገር ግን 2007 ዓ.ም አቶ ጌታቸው እና ቤተሰባቸው ይኖርበት የነበረውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ይገኝ የነበረውን ቤት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤት ከቤቱ እንዲወጡ ማስታወቂያ ለጠፈ። የተለጠፈው ማስታወቂያም 077 ቤት እየኖራችሁ ላላችሁ ሰዎች ከወረዳው ቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤት ጋር ውል አልተዋዋላችሁም፣ ኪራይም እየከፈላችሁ አይደለም፣ ያለአግባብ የመንግሥት ቤት ይዛችኋል የሚል ማስታወቂያ እንደነበር አቶ ጌታቻው ያስረዳሉ።

አቶ ጌታቸውም በወቅቱ ወረዳ ሰባት ቤቶች ልማት





ጽሕፈት ቤት በመሄድ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የሚገኘው ቤት የማካካሻ ቤት ስለሆነ የኪራይ ውል እንዳልተዋዋሉ እና ኪራይ እንደማይከፍሉ ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ መልስ ሊያገኙ አልቻሉም። ይብሱኑ ቤቱ በላያቸው ላይ ታሸገ። በቤታቸው መታሸግ ግራ የተጋቡት አቶ ጌታቸው፣ ጉዳዩን ለወረዳው ፍትህ ቢሮ አቤት አሉ። ይሁን እንጂ አቤቱታቸውን ሊሰማ ፈቃደኛ የነበረ አካል ማጣታቸውን ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ከሁለት አመት በኋላ በ2009 ዓ.ም የወረዳው አስተዳደር አቶ ጌታቸው እና ቤተሰባቸው በሌሉበት የታሸገውን ቤት በመስበር ያለማንም ፈቃድ የቤቱን ዕቃ በማውጣት ቤቱን አከራዩት። የተወሰዱ ሙሉ የቤት ዕቃዎች እስከዛሬ ድረስ የት እንደገቡ እንደማያውቁ አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ።

ማዘጋጃ ቤቱ ለቤቶች ልማት መረጃ ላኩልን ካላቸው እና ቤቶች ልማት ደግሞ ጉዳዩን ኮሚቴ አቋቁመን እኛ እናየዋለን ካሉ ጊዜ ጀምሮ ስለጉዳዩ በየቀኑ እየሄዱ ለቤቶች ልማት ምን ላይ ደረሰ እያሉ ይጠይቁ እንደነበር የሚናገሩት አቶ ጌታቸው፣ ይሁን እንጂ የተቋቋመው ኮሚቴ እዚህ ግባ የሚባል መፍትሄ እንዳላመጣ ጠቁመዋል።

ተስፋ ያልቆረጡት አቶ ጌታቸው፣ ከአዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር ጋር በሚሟገቱበት ሰዓት ለውጡን ተከትሎ ከማካካሻ ቤት ጋር ተያይዞ ለቤቶች አስተዳደር ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መመሪያ ወረደ። መመሪያውም በማካካሻነት የተሰጣችሁት ቤቱ በእጃቸው እስካለ ድረስ በአደራ የሰጣችሁት ቤት ተመላሽ ይሆናል የሚል ነው። ይሁን እንጂ አቶ ጌታቸው በግድ በማካካሻነት ከተሰጡት ቤት ተባርረው ስለነበር ቤቱ በእጃቸው አልነበረም።

ይሁንና ከማካካሻው ቤት የወጣሁት በግዳጅ ነው ሲሉ አሁንም ለአዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር አቤት አሉ። ነገር ግን አዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር ቤቱን በግድ እንደነጠቀ እያወቀ ቤቱ በእጅህ ስለሌለ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው ይናገራሉ።

ተስፋ መቁረጥን አላውቅም የሚሉት አቶ ጌታቸው፣ በማካካሻነት የወሰዱት ቤት በእጃቸው እንደሌለ እና ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው አዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደርን መጠየቃቸውን ይገልጻሉ። ይህን ተከትሎ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደርም «ኮሚቴ ተቋቁሟል፤ ወረዳ ድረስ ሄደን እናጣራለን» የሚል መልስ እንደሰጧቸው ይገልጻሉ።

በማካካሻነት የተሰጠውን ቤት በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 07 ቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤት በጉልበት ቤቱን ሰብረው እንዳስወጧቸው የሚገልጽ ማስረጃ ለተቋቋመው ኮሚቴ ማቅረባቸውን ያስረዳሉ። የተቋቋመው ኮሚቴም በጉለሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 07 የቤት ቁጥር 077 እናንተ ስለመሆኑና ከ1968 እስከ 2007 ዓ.ም መኖራችሁን የሚያሳይ መረጃ ካለ እሱን እንመረምራለን አለ።

ኮሚቴውም ከብዙ ድካም በኋላ ምርመራውን ጨርሶ ቤቱ ለአቶ ጌታቸው እንደሚገባና ከሁለቱ ቤት አንዱን የመመረጥ መብት አላቸው የሚል ውሳኔ ወሰነ የሚሉት አቶ ጌታቸው፣ የኮሚቴው በምርመራ የደረሰበትን ለውሳኔ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ቢሮ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ ለፊርማ ያስገቡታል። ምክትል ሥራ አስፈጻሚ በአስተዳደር የታየውን ወደ ሕግ ክፍል መሩት ።

ይህን ተከትሎ በአስተዳደር የታየውን ወደ ሕግ ክፍል ተመራ ብለው ለዋና ሥራ አስፈጻሚዋ አቤቱታ ማቅረባቸውን አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ። ምክንያቱም በአስተዳደሩ ያለቀን ጉዳይ ወደ ሕግ ክፍሉ መመራቱ ጉዳዩን መልሶ ሊያበላሸው እንደሚችል ቀድመው መገንዘባቸውን ያስረዳሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ በቤቶች አስተዳደር ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ሃብታሙን ማናገራቸውን የገለጹት አቶ ጌታቸው፣ አቶ ሃብታሙም ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማው ከሕግ ክፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ እንዲወስዱ እንዳስገደዷቸው ያስረዳሉ።

ይህን ተከትሎ አቤቱታ አቅራቢው አቶ ጌታቸውም መውሰድ ካለብኝ በኮሚቴ የተወሰነው ውሳኔ ጭምር እንጂ የሕግ ክፍሉን ውሳኔ ብቻ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አልወስድም ማለታቸውን ይገልጻሉ። ኮሚቴው የወሰነውን ውሳኔ ከሕግ ክፍሉ ውሳኔ ጋር አንድ ላይ ላኩልኝ እና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚሰጠውን ውሳኔ በጸጋ እቀበላለሁ በማለት አቶ ሃብታሙን ቢጠይቁም ለጠየቁት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ እንዳልሰጧቸው ይናገራሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ የኮሚቴውን ውሳኔ ለማግኘት ለአንድ ወር ሙሉ አዲስ አበባ ቢሮ መመላለሳቸውን ያስረዳሉ።

በመጨረሻ ጉዳዩ ከአቅማቸው በላይ ሲሆን የሕግ ክፍሉን ውሳኔ ብቻ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር መውሰዳቸውን የሚናገሩት አቶ ጌታቸው፣ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደርም ለምን ይህን ብቻ የሕግ ክፍሉን ውሳኔ ብቻ ይልኩልናል ? ብለው እንደጠቋቸው እና በሕግ ክፍሉ ውሳኔ ብቻ የጠየቁት የይገባኛል ውሳኔ ሊስተናገድ እንደማይችል ገለጹ።

‹የፈሩት ይደርሳል ፤ የጠሉት ይወርሳል› ያሉት አቶ ጌታቸው፣ የሕግ ክፍሉም ከዚህ ቀደም በፍርድ ቤት የተወሰነ ውሳኔ በኮሚቴ ታይቶ ሊቀለበስ አይገባውም የሚል ውሳኔ ማስተላለፉን ይገልጻሉ።

በሚቀጥለው ክፍል ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የተለያዩ አካላትን ምላሽ እና መመሪያዎች ምን ይላሉ የሚለውን ዘገባ ይዘን እንቀርባለን፤ እስከዚያው ቸር እንሰንብት።

# «ከተበላሸው ትናንት የተሻለ ነገ፤ ያማረ ነገ፤ የተዋበ ነገ፤ ተስፋ ለትውልድ የሚሰጥ ነገን መፍጠር እንችላለን»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**/ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ « ጦርነት ይብቃ ሰላምን እናጽና» በሚል የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በሂደቱ አስተዋጽዖ ሳደረጉ ሁሉ የእውቅና እና ምስጋና መርሐ ግብር ላይ ያስተላለፉት መልዕክት ሙሉ ቃል/**



የተከበሩ ሙሳ ፋኪ መሃመት የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበር፤ የተከበሩ አባሳንጆ የዚህ የሰላም ሂደት ሰብሳቢና ልዩ ሚና የተጫወቱ አባት፤ የተከበሩ ኡሁሩ ኬኒያታ የቀድሞ የኬኒያ ፕሬዚዳንት፤ የተከበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት ኡማላንቦ፤ የተከበሩ የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ፓንዶር፣ የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፤ የተከበሩ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር፤ የተከበሩ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት፤ የተከበሩ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ፤ የተከበሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በኢፌዴሪ ወገን ይህን የሰላም ቡድን የመሩ ሽልማታቸውን በጓዳ የተቀበሉ አቶ ደመቀ መኮንን፤ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ፤ የተከበራችሁ የክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች፤ በተለየ መንገድ የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳና ከትግራይ የመጣችሁ ልዑካን፤ የሀገር ሽማግሌዎች፤ የእምነት አባቶች፤ በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ ታዳሚዎች፤ ፈጣሪ እንኳን ይህቺን ቀን በጋራ አሳየን፡ እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ። እንደዚህ ያለውን ድንቅ ቀን እንዲሁ አቅልሎ መቀበሉ ተገቢ አይደለም። ካለፍንበት መከራ አንጻር ይህንን ቀን የሰጠን፤ ይህንን ቀን እንድናይ ያደረገንን ፈጣሪ መላው ኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያመሰግን ከአደራ ጭምር ላሳስብ እወዳለሁ።

ጠብ አቁሞ ሰላም ለመፍጠር ፤በቂ ያልሆነ ምክንያት፤ ትክክለኛ ያልሆነ ጊዜ የለም። ሰላም ምክንያት አይፈልግም። ሰላም የተለየ ጊዜም አይፈልግም። በዚህም ምክንያት ዛሬ እየሆነ ያለው የሰላም መቋጫ የምስጋናና የአዲስ ምዕራፍ መጀመሪያ ማብሰሪያ ዕለት ምክንያትም የተገደበ ጊዜ ሳይሆን ዛሬውኑ መሆን ያለበት እንደሆነ ይሰማኛል።

ጥላቻ ያፈርሳል፣ ያናቁራል፣ ያገፋፋል። ፍቅር ይገነባል፣ ያሳስባል፣ ያስቃል። ጦርነት ያወድማል፣ ይገላል፣ ያፈርሳል። ሰላም ያለማል፣ ያበለጽጋል፣ ወጥቶ መግባትን በቀለለ መንገድ እንዲቻል ያደርጋል። ጦርነት ጨለማ ነው። ጦርነት ክፉ ነው፡፡

ከአፍ የሚወጣው፤ ከአፈሙዝ የሚወጣው ውስጥንና ሥጋን የሚገድል ነው። ሰላም ብርሃን ነው። ሰላም የነገር ሁሉ መጀመሪያ ነው። ስለሆነም ለዚህ ሰላም ቀን እንድንበቃ ያደረጋችሁ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ወዳጅ ሀገራት፣ ኢትዮጵያ ከነበረችበት ጨለማ ወደሚገባት ብርሃን ለመሸጋገር ፈቅዳ የጀመረችበት ዕለት ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን በቂ የጦርነት ታሪክ አለን። የበቃና የሚነገር የሰላም ታሪክ ግን የለንም። ጦርነት በሁለት ሰላሞች መካከል የሚፈጠር ሁኔታ መሆን ሲገባው፤ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ግን ሰላም በሁለት ጦርነቶች መካከል የሚገኝ እፎይታ ብቻ ሆኗል። የረዘመ ሰላም አልፎ አልፎ ግጭት የተለመደ ቢሆንም ለእኛ ኢትዮጵያውያን ግን የበዛ የማይፈለግ ጎጂ ጦርነትና አልፎ አልፎ የሚገኝ የሰላም እፎይታ ብቻ ሆኗል ።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያንና ታዳሚዎች፤ ሁለት ዓመት ከመዋጋት ሃያ ዓመት መወያየት ይሻላል። ሁለት ዓመት ስንዋጋ ብዙ እናወድማለን። ብዙ እንገድላለን፤ ውስጣችን ይሞታል የመፍጠር አቅማችን ይዳከማል።ሃያ ዓመት ስንወያይ የፈለግነው የተመኘነው በአጭር ያልተከወነ ይሆን ይሆናል ነገር ግን በሂደቱ ሰው ሳንጎዳ ንብረት ሳናወድም ለመማር እድል የሚሰጥ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን እንንቃ፡፡

በውይይት፣በምክክር ችግሮቻችንን መፍታት የሥልጣኔ ሀሁ እንደሆነ እንገንዘብ። ከምክር ይልቅ መከራ የሚመክረው ሕዝብ አንሁን። እኛ ኢትዮጵያውያን በምክክር በውይይት ችግርን መፍታት ተስኖን መከራ፣ በሚያስከፋ ሁኔታ የሚያስተምረን ሞኝ ሕዝቦች አንሁን። በዚህም ብዙ እናጣለንና።

ትናንት ብዙ አምልጦናል፤ ብዙ የተበላሹ ነገሮች አሉ። ነገር ግን ከተበላሸው ትናንት የተሻለ ነገ፤ ያማረ ነገ፤የተዋበ ነገ፤ ተስፋን፤ ለትውልድ የሚሰጥ ነገን መፍጠር እንችላለን። ትናንትናን እያሰብን ቁስል እያከክን የምንቆም ሳይሆን፤ ትናንትናን ተሻግረን የተሻለ ነገር ለመፍጠር የምንተጋ የምንሥራ እንድንሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ጦርነት ማስቀረት፣ ስድብ ማስቀረት፣ መገፋፋትን ማስቀረት፤ የይቅርታ ዋንኛ ተልዕኮ ነው። እርቅ ግን ማረም ነው። ዛሬ ይቅርታና እርቅ ስለሆነ ማስቆም ብቻ ሳይሆን ወደኋላ የተበላሸውንም ማረም ይጠበቅብናል። የተሰበረን መጠገን፣ የቆሰለን ማከም፣ መብል የተቸገረን ማብላት፣ ትናንትናን የተሻለ ፍቅር ማደስና ማስቀጠል የሚያስችል መሠረት መጣል ይኖርብናል።

የተከበራችሁ ታዳሚያንና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በውጊያ የላቁ፣ በጀብዱ የደመቁ በሀገር ፍቅር ያሸበረቁ፣ ለሀገር የሚበቁ ዘወትር የነቁ ፣ኢትዮጵያን በልባቸው ያነገሱ፣ አይተኬ ሕይወታቸውን እንኳን በኢትዮጵያ የማይደራደሩ፣የበቁ የፀጥታ ኃይሎች አሉን።

በሙያቸው፣ በእውቀታቸው፣ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን እንዲጠብቁ ከአፈሙዝ ጋር የሚያያዘውን ሥራ ለእነሱ እንተውላቸው። ለነቁ፣ ለበቁ ፣ሀገር ለሚወዱ የፀጥታ ኃይሎች ዲሞፍቶር ትተን እኛ ሞፈር እናንሳ። ሁሉም ዲሞፍቶር አንሺ ከሆነ ሞፈር የሚጨብጠው እጅ ያጣል።

ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ሞፈር ነው። በርግጥ የሚጠብቋት የተማሩ የነቁ ዲሞፍቶር የጨበጡ የሚያስፈልጓት ቢሆንም ብዙዎቻችን ግን ሞፈር የምንጨብጥና ሞፈር የሚጨብጡት የምንደግፈ ብንሆን ከልመና ነጻ እንወጣለን።

ማንዴላ "በሕይወቴ ተሸንፌ አላውቅም" ይላሉ።" በገጠሙኝ ፈተናዎች ባለፍኩባቸው ተግዳሮቶች አንዳንዴ አሸንፌለሁ ፤ብዙ ጊዜ ግን ተምሬለሁ" ይላሉ። የገጠመን ፈተና ያሸንፍንበት ብለን የምንኩራራበት ባይሆንም እንደ ኢትዮጵያውያን የተማርነበት፣ የምንማርበት የምንሻገርበት ሊሆን ይገባል ።

እጅግ በቂ የሆነ ትምህርት ያገኘንበትን የጥፋት ጊዜ ስላሳለፍን ከእንደዚህ አይነት ተግባር ተቆጥበን፣ ተምረን ልጆቻችንና የሚቀጥለው ትውልድ ያማረች ያሸበረቀች ኢትዮጵያን መውረስ እንዲችል፤ ከጥላቻ ከመገፋፋት ከመዋጋት ራቅ እንድንል በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ኢትዮጵያውያን አንድ አባባል አላቸው፤ "ሲታረቁ ከሆድ፣ ሲታጠቡ ከክንድ" ይላሉ። እኛ ስንዋጋ ከልባችን ነበር የተዋጋ ነው፤ ከዛሬ ጀምሮ ግን ከልባችን መታረቅ ይኖርብናል። ኢትዮጵያውያን በጦርነት ጀግኖች መሆናችንን ዓለም ይመሰክራል። በሰላም ጀግኖች መሆናችንን ግን ከልብ መታረቅ ብቻ ሳይሆን የተጎዳው ሁሉ ወገኔ ነው ብለን በሙሉ ልብ በአንድነት እንድንሠራ ያጎደልነውን፣ ያበላሸነውን፣ በአጠረ ጊዜ እንድንሞላ ሁላችሁንም በታላቅ ትሕትና ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ።

ዛሬ የመረጃ ምንጭ ብዙ ነው። ብዙ ሰዎች መረጃ ማመንጨት ይችላሉ፤ በዚህም የተነሳ ጠዋት ተገናኝታችሁ ከተስማማችሁ በኋላ ከሰዓት ሰዎች ሀሳባቸውን ይቀይራሉ።ውሳኔ መነሻው መረጃ ነው። ኢንፎርሜሽን ነው ፤ ኢንፎርሜሽን በጣም በስፋት በሚሰራጭበት በዚህ ዓለም ጠዋት ያገኛችሁት ወንድማችሁ ማታ ሌላ አቋም ሊይዝ ይችላል።

በዚህ ዓውድ ውስጥ የምንኖር ትውልዶች ልንማር የሚገባው ጉዳይ ዛሬ የሚያዋጣው መቻቻል ብቻ ነው። ምክንያቱም በየቀኑ የሚቀያየር ባሕሪ ስላለ፤ በመቻቻል፣ በመደማመጥ በመወያየት የበለጠውን የላቀውን በመመኘትና ለዚህ በመትጋት መሥራት ይኖርብናል። በተለዋዋጭ ዓለም እና በበዛ ኢንፎርሜሽን የአቋም ልዩነት ሲፈጠር ሰክኖ መወያየት ፣ መነጋገር ያስፈልጋል።

አቶ ጌታቸው ሰላሙን ያመጣነው ጀግነን ነው ብሏል። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት አቶ ጌታቸውን የምጠይቀው ጀግኖ ወደ ባሕር ዳር እንዲሄድና ወንድሞቹን ማቀፍ እንዲችል ነው፡፡ ዶክተር ይልቃልን የምጠይቀው ጀግኖ ወደ መቀሌ እንዲሄድና ወንድሞቹን እንዲያቅፍ ነው። ሰላም እንዲሁ በቀላል የሚገኝ አይደለም። መሥራት፣ መትጋት፣ መጀገን ይፈልጋል።

የተከበረው የትግራይ ሕዝብ ከተከበረውና ከወንድሙ የአማራ ሕዝብ ጋር ጠንካራ የደም ትስስር ያለው ቢሆንም፤ በፖለቲካ ብልሽት ምክንያት የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት አቶ ጌታቸው፣ ዶክተር ይልቃል መጀገን ይጠበቅባቸዋል። አቶ አወል በዚህ አይጠረጠሩም ብዬ ነው።

ዛሬ ለኢትዮጵያ እጅግ አስደሳች ቀን ነው። ከዛ የጦርነት ነጋሪት ፉከራ፣ጥፋት ወጥተን፣ሰላም መልሶ ግንባታን የምንነጋገርበት ቀን ነው። ይህ ለእኛ ደስታ የሆነው ቀን እጅግ ለምንወደው ለደጉ፤ በቸገረን ጊዜ ሁሉ መጠጊያችን ለሆነው ኢትዮጵያን አብዝቶ ለሚወደው ለሱዳን ሕዝብ ይህችን ቀን ማየት እንዲችል ያለንን ከፍተኛ ምኞት እየገለፅኩ ወንድሜ ጄኔራል ቡርሃን እና ወንድሜ ጄኔራል አህሚቲ ከኢትዮጵያውያን ተምረው ሰክነው፣ ተነጋግረው፣ በሱዳን ያጋጠመውን ያልተገባ መገዳደል እንዲያስቆሙ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ ላቀርብላቸው እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ለወንድም ሕዝቦች ሰላም የምትመኝ ሰላም አስከባሪ የምትልክ ብቻ ሳትሆን፤ ለሱዳን 50ሺ ኩንታል ስንዴና በርከት ያሉ መድኃኒቶች ለመላክ ኢትዮጵያን ኤይድ ወደ ካርቱም ለመሄድ የተዘጋጀ መሆኑን ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ በደስታ ማብሰር እፈልጋለሁ።

የሱዳን ሕዝብ ከወንድም የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ይፈልጋል። ኢትዮጵያውያን እንደ ድሮው ማንነታችን ተርፎን ሳይሆን ከጎደለ ማንነታችን በማካፈል ወንድም ሕዝብን ለማጽናናት ጊዜው አሁን ስለሆነ እኛ ኢትዮጵያውያን ለማስታረቅ፤ ለመርዳት፤ ከፍተኛ ዝግጁነት እንዳለን አውቀው የሱዳን አመራሮች ይሄን መሰል ፕሮግራም በካርቱም ለማዘጋጀት እንዲታደሉ ያለኝን ታላቅ ተስፋና ምኞት ልገልፅላቸው እወድዳለሁ።

በሚቀጥለው ሳምንት ሁለት ኩነቶች ይከወናሉ። አንደኛው የሁሉም ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት እየተመሩ ወደ መቐሌ ይሄዳሉ። የሁሉም ክልል ርዕሰ መስተዳድሮች መቐሌ የሚሄዱት ያነቡ ዓይኖችን ለማበስ፤ የተበላሹ፣ የፈረሱ ቦታዎችን ለመጠገን፤ ክልሎች እንደ ወንድም ሕዝቦች ካላቸው ለማጋራትና ይሄን የሰላም ጅማሮ በተግባር ለማስቀጠል ነው፡፡ በሚቀጥሉት ቀናት ወደ መቐሌ የሚደረገው ጉዞ ዛሬ የምናደርገው ንግግር የተግባር ማስጀመሪያና ወንድም የትግራይን ሕዝብ ከጎኑ መሆናችንን፤ መሆናቸውን ሁሉም ክልሎች የሚያሳዩበት ዕለት ስለሆነ ልክ እንደ ዛሬው ቀን በከፍተኛ ጉጉት የምንጠብቀው ይሆናል።

ሁለተኛው ከሸኔ ጋር የሚደረገው ድርድር ከነገ ወዲያ በታንዛንያ ይጀመራል። ይሄን ድርድር የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ አብዝቶ ይፈልገዋል። በዚህ ድርድር የሚሳተፉ ወገኖች ሁሉ የዛሬዋን ቀን እያሰቡ፤ከግጭት፤ ከጦርነት እንደማናተርፍ አውቀው ሕግና ሥርዓት ተከትለን፣ ይቅር ተባብለን ሀገራችንን በጋራ ማነፅና መገንባት እንድንችል፤ የወለጋ ሕዝብ አሁን ካለበት ስቃይ እፎይ ማለት እንዲችል ሁሉም ወገን የበኩላቸውን እንዲያደርጉ ከወዲሁ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም የኛ የሰላም ሂደት እንዲሳካ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉ የወዳጅ ሀገራት፤ የአፍሪካ ኅብረት፣ ኢጋድ እንዲሁም አንዳንድ ግለሰቦች ከሁሉ በላይ የቲፒኤልኤፍ አመራሮች፣ የብልጽግና አመራሮች መላው የትግራይ ሕዝብ፣ የአማራ ሕዝብ፣ የአፋር ሕዝብ፣ የሶማሌ ሕዝብ፣ የኦሮሚያ ሕዝብ፣ የሲዳማ ሕዝብ፣ የደቡብ፣ ሁሉም ብሔሮች፣ (ጉራጌ ስልጤ፣ወላይታ፣ ሃድያ፣ ከንባታ፣ ዳሰነች፣ ዳውሮ፣ ኮንታ) የተቀሩትን በሙሉ የጋምቤላ ሕዝብ፣ የደቡብ ምዕራብ ሕዝብ፣ የቤኒሻንጉል ሕዝብ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ላደረጋችሁት ድጋፍና ጸሎት፤ ምኞት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥትና በራሴ ስም በተለይም የኢትዮጵያ እናቶች ለነበራችሁ ጭንቀትና ጸሎት ያለኝን ከፍተኛ ምስጋናና አክብሮት በዚህ ታሪካዊ ቀን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ውድ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ ኢትዮጵያ ትፀናለች፣ ኢትዮጵያ ትቀጥላለች፤ ኢትዮጵያን የሚያስቆማት ምንም ኃይል የለም፤ ኢትዮጵያን የሚያስቆማት ኃይል የኛ መጠላላት ብቻ ነው። ከዛሬው ቀን እንማር የማይወደድ ፣የማይፈለግ የኢትዮጵያ ክፍል የለም፡፡ አንዳንዶች ኢትዮጵያ ትገነጣጠላለች ወይም አንዳንዶች ይገነጠላሉ ይላሉ ፤ኢትዮጵያ አትገነጠልም ጸንታ ትቀጥላለች። ይልቁንም ለልማቷ፣ ለመጽናቷ ለአንድነቷ የሚያስፈልጋትን ፤የቀራትን ለማግኘት አብዝታ ትሠራለች።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ!**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሀገር ምርትን የመጠቀም ችግር የግንዛቤ ወይስ.....?

ቦጋለ አበበ

ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ ከምታቀርበው ምርት ይልቅ ከውጭ ገበያ የምትሸምተው እንደሚልቅ ይታወቃል። ይህ በዋናነት የሆነው የሀገር ውስጥ ምርት አቅርቦት ከተጠቃሚው ፍላጎት ጋር ባለመጣጣሙ ይሁን እንጂ፣ ዜጎች የአገራቸውን ምርት የመጠቀም ዝቅተኛ ልምድ ያላቸው መሆኑም ተጨማሪ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ማኅበረሰቡ ለአገሩ ምርት ያለው ዝቅተኛ ግምት አገሪቱን የውጭ ሸቀጥ ማራገፊያ ከማድረጉም በላይ፣ በኢኮኖሚ በኩልም በከፍተኛ ደረጃ የውጭ ጥገኛ እንዳደረጋት አይካድም። ይህም በውጪ ምንዛሪም ረገድ ከምታስገባው ይልቅ የምታወጣው እንዲበረክት በማድረግ ተደራራቢ ችግሮችን እንድትጋፈጥ አስገድዷታል።

በኢትዮጵያ ከሚመረቱ ምርቶች ውስጥ ጥራታቸው የዓለም ገበያ መስፈርትን ያሟላና ዋጋቸውም ተመጣጣኝ የሆኑ ቢኖሩም፣ ማኅበረሰቡ የአገሩን ምርት መጠቀም ላይ ያለው አመለካከት ዝቅ ያለ በመሆኑ፣ በብዛት ለምርቶቹ ቅድሚያ ሲሰጥ አይስተዋልም።

ከሀገር ቤት ምርቶች ይልቅ የውጪ ምርቶች በመጠቀም ረገድ እንደ ማኅበረሰብ ትልቅ ችግር መኖሩ አይካድም። ይህ ችግር ግን ማኅበረሰቡን በሚመሩ ፖለቲከኞች፣አርቲስቶችና ሌሎች ታዋቂ ሰዎችም በስፋት እንደሚስተዋል በየጊዜው መታዘብ ይቻላል። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት(ካልተሳሳትኩ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ) ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎቻቸውን ሰብስበው ያነሱትን ጉዳይ ላስታውስ። የሀገር መሪው የሥራ ኃላፊዎቹን በተሰበሰቡበት "ሀገሬን እወዳለሁ ትላላችሁ፣ ሀገርን መውደድ የሚጀምረው የሀገር ውስጥ ምርቶችን በመጠቀም ነው፣ እስቲ ሁላችሁም ዝቅ ብላችሁ የተጫማችሁትን ጫማ ተመልከቱ?" ብለው ይጠይቃሉ። እውነትም ጎንበስ ብለው ጫማቸውን ሲመለከቱ አንዳቸውም የሀገር ውስጥ ምርት አልተጫሙም። ሁሉም ከጫማ እስከ ሱፍና ሸሚዝ የለበሱት የጣሊያን ምርቶችን ነበር።

በእርግጥ እንደ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አይነት የኢትዮጵያ የቀድሞ መሪዎች ሀገር ውስጥ የተሠሩ የካኪ ልብሶችን በማዘውተር ለሕዝብ አርአያ ለመሆን ያደረጉትን ጥረትም እዚህ ጋር ማስታወስ ይቻላል። ይህ ጥረት ግን የአንድ ወቅት አጀንዳ ከመሆን አልፎ አያውቅም። ተፅዕኖ ፈጥሮም በሕዝብ አስተሳሰብ ላይ ለውጥ አላመጣም። በእርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ቢሆን አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች፣አርቲስትና ታዋቂ ሰዎች ወደ ቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ሲሉ በሀገር ባሕል አልባሳት እያጌጡ ማየት ተለምዷል። ይህ ግን በብዛት የሚያደርጉት በሀገር ባሕል ከመኩራት አንፃር እንጂ በሀገር ምርት ከመኩራት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ከባድ ነው። ምክንያቱም ለሆነ ፕሮግራም የሀገር ባሕል ልብስ መልበስና በአዘቦት ቀናት የሀገር ውስጥ ዘመናዊ አልባሳት ሞልተው እያሉ በውጪ ሱፍና ከራቫት ማጌጥ ለየቅል ናቸውና። ይህ የሚያሳየው በሕዝብ ብቻ ሳይሆን ተፅዕኖ ፈጣሪ በሆኑ ሰዎች ዘንድም የአስተሳሰብ ችግሩ እንዳልተቀረፈ ነው።

የምሥራቅ እስያ አገራት የሆኑት እንደነ ቻይና፣ ጃፓን፣ ታይላንድ እና የመሳሰሉት ከምዕራባውያን ሀገራት የሚደርስባቸውን ጫና ለመመከትና ሉዓላዊነታቸውን ለማስጠበቅ ትልቁ መፍትሔ ኢኮኖሚያቸውን ማሳደግ መሆኑን በመረዳት፣ የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም መጀመራቸው ዛሬ ለደረሱበት የተሻለ አቅም ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳበረከተላቸው ይነገራል።

‹‹Asian Tigers›› በመባል የሚታወቁትና በዚሁ በምሥራቅ እስያ ክፍለ ዓለም የሚገኙት ሲንጋፖር፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን እና ሆንግ ኮንግም የፈጣን ዕድገታቸው ዋነኛ ምስጢር የሀገራቸውን ምርት፣ ቴክኖሎጂና ዕውቀት፣ እንዲሁም ሌሎች ከሀገራቸው ጋር ተያያዥ የሆኑ ውጤቶችን ለማሳደግና ለመጠቀም ያሳዩት ቁርጠኝነት ነው ተብሎ ይታመናል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት ሕንዶች ናቸው። ሕንዳውያን እንኳን ሀራቸው ውስጥ እየኖሩ በውጪ አገራትም ኑሯቸውን ቢያደርጉም ከሀገራቸውን ምርት ውጪ በተለይም በአልባሳት ረገድ አለመጠቀምን እንደ አንድ የሕይወታቸው መርሕ አድርገው እንደሚቆጥሩ ተመስክሮላቸዋል። በኢትዮጵያ በርካታ ሕንዳውያን በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ዩኒቨርስቲዎች ለማስተማር ኑሯቸውን እዚሁ ማድረጋቸው ይታወቃል። እነዚህ ሕንዳውያን እንኳን አልባሳትን ቀርቶ የሚያጨሱትን ሲጋራ ሳይቀር ከአገራቸው ምርት ውጪ "ወይ ፍንክች" እንደሚሉ በቅርብ የሚያውቋቸው ይመሰክራሉ።

ወደ እኛ አገር ስንመጣ በበርካቶች ዘንድ አንበሳ ጫማ ማድረግ እንኳን የኋላ ቀርነት ምሳሌና መበሻሸቂያ ሲሆን በብዙ አጋጣሚዎች መታዘብ ይቻላል። አስገራሚው ጉዳይ ግን ለውጪ ምርቶች ብቻ ተገዢ የሆኑ ሰዎች ተመልሰው ስለ ሀገር ወዳድነትና ስለ ሀገር ፍቅር ሕዝብን ሲመክሩና ሲያስተምሩ ማየት ነው። ሀገሬን እወዳለሁ የሚል አንድ ሰው ይህችን ትንሽ ነገር ለሀገሩ ማድረግ ካልቻለ እንዴት ለሌላው ነገር ይታመናል?።

ከሀገር ውስጥ ምርቶች ያነሰ ጥራትና የበለጠ ዋጋ ያላቸው ምርቶች ከውጭ አገር የተገኙ ስለሆኑ ብቻ እንደ ልብ ሲሸጡ ማየት ብርቅ አይደለም። ሌላው አስገራሚ እውነታ ከውጪዎቹ ይልቅ በተቃራኒው የኢትዮጵያ ምርቶች ሌላ አገር ገበያ ውስጥ አዲስ የገበያ ሥያሜ ተሰጥቷቸው በውድ ዋጋ መሸጣቸው ነው። ይህ አላዋቂነት እንጂ ሌላ ሊባል አይችልም።

ይህ ዜጎች የሀገርን ምርት ያለመጠቀም ልማዳቸው፣ የአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዳያድጉ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እንዳይኖር እና የሥራ ዕድል እንዳይስፋፋ በማድረግ በአጠቃላይ ሀገሪቱን በብዙ መልኩ የሚጎዳ አስተሳሰብ ነው። እኛ ግን አንድም ይህን ካለመገንዘብ ለሀገር ውስጥ ምርቶች ግድ የለንም። ግንዛቤው አላቸው የሚባሉ ሰዎችም አገራቸውን እንደሚወዱ የሀገር ምርት በመሸመት ለማሳየት ወይ ቸልተኛ ናቸው ወይ ደግሞ ፍላጎቱ የላቸውምና ሁላችንም እናስብበት።

# ዓለም አቀፍ



## ኢራን መንግሥትን የሚቃወሙ ታዋቂ ግለሰቦችን ለመቅጣት ኮሚቴ ማቋቋሟን ሰነዶች አጋለጡ

ኢራን ጸረ መንግሥት የተቃውሞ ሰልፎችን የሚደግፉ ታዋቂ ግለሰቦችን ለመቅጣት ምስጢራዊ ኮሚቴ ማቋቋሟን ሾልከው የወጡ ሰነዶች እንዳጋለጡ ቢቢሲ ዘግቧል።

ቢቢሲ ሾልከው የወጡ ሰነዶችን እንዳገኘ ገልጾ፤ በኢራን ከተከሰተው አለመረጋጋት ስድስት ቀናት በኋላ የተቋቋመው ኮሚቴ የ141 ታዋቂ ሰዎችን ስም ዝርዝር የያዘ ደብዳቤ ለኢኮኖሚ ሚኒስቴር መላኩን አስታውቋል።

ኮሚቴው"የታዋቂ ግለሰቦች ግብረ ኃይል" የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ሊቀ መንበሩ የባሕል እና እስላማዊ መመሪያ ሚኒስትሩ መሐመድ መህዲ እስማኢሊ ሲሆኑ በአውሮፓ ኅብረትም ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ፈጽመዋል በሚል ማዕቀብ እንደተጣለባቸው ቢቢሲ ጠቁሟል።

ኮሚቴው በደብዳቤው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የነዚህን ታዋቂ ግለሰቦች የግብር ተመላሽ አጣርቶ ያልተገለጸ እርምጃ እንዲወሰድባቸውም ጠይቋል።

ኮሚቴው የኢራንን ሁከት በማቀጣጠል ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል የተባሉ 141 ታዋቂ ግለሰቦችን የግብር ምላሽ እንዲመረምርና በሕጉ መሠረት የሚጠበቁ ገደቦች እንዲተገብር ለኢኮኖሚ ሚኒስቴር ትዕዛዝ ማስተላለፉ ተጠቅሷል።

በዝርዝሩ ውስጥ ታዋቂው የእግር ኳስ ተጫዋች አሊ ዴኢ እና ታዋቂዋ ተዋናይት ታራኔህ አሊዶስቲ ተካትተዋል። በተጨማሪ ታዋቂዎቹ የፊልም ባለሙያዎች አስጋሪ ፋርሃዲ፣ ፔጋህ አሀንጋራኒ፣ ማኒጄህ ሄክማት፣ ባርዙ አርጆማንድ እና ሻሂን ሳማድፑር፣ እንዲሁም የቀድሞ የቴሌቪዥን አቅራቢ ኢህሳን ካራሚ እንደሚገኙበት ቢቢሲ ዘግቧል።

እነዚህ ግለሰቦች ባለፉት ሰባት ወራት ውስጥ ተቃዋሚዎች ያነሷቸውን የነጻነት ጥያቄዎች መደገፋቸውን ተከትሎ የኢኮኖሚ ማዕቀብ፣ የጉዞ እገዳ ወይም እስር ካጋጠማቸው በደርዘን ከሚቆጠሩ አርቲስቶች፣ ስፖርተኞች እና የማኅበራዊ ተጽእኖ ፈጣሪዎች መካከል መሆናቸውን ቢቢሲ ገልጿል።

በኢራን የራስ መሸፈኛዋን በአግባቡ አልለበሸም ተብላ በፖሊስ ቁጥጥር ስር በነበረችበት ወቅት በደረሰባት ድብደባ የሞተችው ማህሳ አሚኒንም ሞት ተከትሎ ነው በኢራን ብሔራዊ ቁጣ ተቀስቅሷል።

የፀጥታ ኃይሎች በወሰዱት የኃይል እርምጃ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲሞቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ታስረዋል። ኢራን ሕዝባዊ ተቃውሞው በውጭ ሃገራት የተቀሰቀሰ አመጽ አድርጋም እንደምታየው አስታውቃለች።



## በሄይቲ በፖሊስ ሲፈስጉ የነበሩ 13 የአንድ ቡድን አባላት ተገደሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሄይቲ በፖሊስ ሲፈለጉ የነበሩ 13 ተጠርጣሪ የወንበዴ ቡድን አባላት መገደላቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ተጠርጣሪዎቹ ሰኞ ዕለት በፖርት ኦ ፕሪንስ ተቃጥለው ከመገደላቸው በፊት የማኅበረሰቡ አባላት በኅማ ክፉኛ እንደበደቧቸው ተገልጿል። ፖሊስ እንዳስታወቀው ይህ ከመሆኑ በፊት ከተጠርጣሪዎቹ ላይ መሣሪያቸውን እንደወሰዱባቸው ነው። የማኅበረሰቡ አባላት ተጠርጣሪዎቹን እንዴት ሊይዟቸው እንደቻሉ ግን ፖሊስ አላብራራም። በሄይቲ እ.አ.አ. ሐምሌ ወር 2021 ፕሬዚዳንት ጆቨኔል ሞኢስ ከተገደሉ በኋላ ሕገ ወጥነት ተበራክቷል።

የተባበሩት መንግሥታት ሰኞ እለት በወጣው ሪፖርት እንዳለው በዋና መዲናዋ ያለው የደኅንነት ችግር በጦርነት ውስጥ ካሉ ሀገራት ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ደርሷል። የታጠቁ ወንበዴዎች የያዙትን ግዛት የማስፋፋት ፉክክሩ በመቀጠሉ ከፖሊስ ጋር እና ከተቀናቃኝ የወንበዴ ቡድኖች ጋር የሚፈጠር ግጭት ተደጋጋሚ በመሆኑ የበርካታ ሰላማዊ ሰዎችን ሕይወት መቅጠፉንም ሪፖርቱ አክሏል።

እንደ ተመድ ከሆነ ከአውሮፓውያኑ ሚያዚያ 14 እስከ 19 ባሉት አምስት ቀናት ብቻ 18 ሴቶች እና ሁለት ሕጻናትን ጨምሮ ወደ 70 የሚጠጉ ሰዎች በወንበዴዎች በተፈጸመ ጥቃት ተገድለዋል። በርካታ ትምህርት ቤቶች እና የጤና ተቋማት የተዘጉ ሲሆን ጥቃቱ ሌሎች የማኅበረሰብ አገልግሎቶችንም አስተጓጉሏል። የሄይቲ ሕዝቦች በአስርት ዓመታት ውስጥ አስከፊ በሆነው የሰብዓዊ መብት ቀውስ እና በአስቸኳይ የሰብዓዊ እርዳታ እጦት መሰቃየታቸውን ቀጥለዋል ብሏል ሪፖርቱ።

ከፕሬዚዳንት ሞኢስ ግድያ በኋላ የካሪቢያን አገሯ በጠቅላይ ሚኒስትር አሪል ሄንሪ እየተመራች ሲሆን አሁን ከዋና ከተማዋ 60 በመቶ የሚገመተውን አካባቢ የሚቆጣጠሩትን የወንበዴ ቡድኖች ግን መቆጣጠር ተስኗቸዋል።

ሄንሪ እና የተመድ ባለሥልጣናት ፖሊስ ከወንጀለኛ ቡድኖች ጋር የሚያደርገውን ፍልሚያ ለማገዝ በአካባቢው ዓለም አቀፍ ኃይል እንዲሠማራ በተደጋጋሚ ጠይቀዋል። ሆኖም እስካሁን ይህንን ኃላፊነት የተቀበለ አገር የለም። አሜሪካ፣ ካናዳ ኃላፊነቱን እንድትወስድ ለማግባባት ብትሞክርም ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ እስካሁን አልተቀበሉትም።

ሄንሪ ለረጅም ጊዜ የተራዘመው ምርጫ እንዲካሄድም የጸጥታ ሁኔታን ማረጋገጥ ቁልፍ ነው ብለዋል።

# የቆዳው ኢንዱስትሪ በመነቃቃት ጎዳና

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በእንስሳት ሀብቷ ከፍተኛ አቅም እንዳላት የሚነገርላት ኢትዮጵያ ሀብቷን በአግባቡ መጠቀም አለመቻሏም እንዲሁ በስፋት ይገለጻል። ከእንስሳት ሀብቷ የምታገኘውን ስጋና የእርድ ተረፈ ምርቶች ወደ ውጭ ገበያ በመላክ በሚሊዮኖች ዶላሮች የሚቆጠር ገቢ እያገኘች ብትሆንም፣ ካላት እምቅ የእንስሳት ሀብት አኳያ ሲታይ ገቢው ዝቅተኛ የሚባል መሆኑ ይገለጻል።

አገሪቱ ቀደም ሲል ለውጭ ገበያ ከሚቀርቡ የግብርና ምርቶች አኳያ ከቡና ቀጥሎ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ታገኝ የነበረው ጥሬ ቆዳ ለውጭ ገበያ በማቅረብ እንደነበረ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህን ገቢ ለማሳደግ በጥሬ ቆዳ ላይ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ ማቅረብ ውስጥ ተገብቶም ነበር። በሁለቱም የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የእቅድ ዘመኖች በቆዳው ላይ በስፋት በመሥራት ከቆዳው ዘርፍ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ቢታቀድም እቅዱ ግን አልተሳካም። ከዚህ ይልቅ የጥሬ ቆዳ ዋጋ እየቀነሰ መጥቶ ቆዳ ገዥ እያጣ እንደ ዋዛ እየተጣለ ይገኛል።

በእሴት ሰንሰለት ውስጥ በተለያየ ዘርፍ ሰፊ ቁጥር ያለውን የሰው ኃይል በማሳተፍ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ እገዛ እያደረገ እንደሚገኝ የሚነገርለት የቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት ትኩረት እያገኘ መሆኑ ይነገራል።

ሰሞኑን ለ13ኛ ጊዜ የመላው አፍሪካ ዓለም አቀፍ የቆዳ ንግድ ትርዒት በሚሊኒየም አዳራሽ ለሦስት ቀናት ተካሂዷል። በቆዳ ዘርፍ የተሰማሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው አንጋፋና አዳዲስ ድርጅቶችም በንግድ ትርዒቱ የተሳተፉ ሲሆን፤ የንግድ ትርኢቱ ፋይዳ ብዙ ስለመሆኑም ተናግረዋል።

በአንበሳ ጫማ ፋብሪካ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አጠቃላይ የአንበሳ ጫማ መደብሮች ኃላፊ አቶ ቅዱስ በላይ ፋብሪካው በቆዳ ምርቱ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑን ጠቅሰው፣ እንዲህ ያሉ የግንድ ትርዒቶች የገበያ ትስስር ለመፍጠርና አገርን ለማስተዋወቅ እንደሚጠቅሙ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ ጫማ፣ ቦርሳ፣ ቀበቶ፣ የመከላከያ ጓንትና የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን እያመረተ ለገበያ ያቀርባል። ከዚህ ቀደም ቆዳውን ከተለያዩ ቆዳ አቅራቢ ድርጅቶች በመግዛት የሚያመርተው ፋብሪካው፣ በአሁኑ ወቅት የራሱን ቆዳ ፋብሪካ በባህርዳር አቋቁሟል። ይህም ምርቱን በስፋትና በጥራት ሳይቆራረጥ ለማምረት ያስችለዋል።

የቆዳ ኢንዱስትሪው በአገሪቱ ትልቅ አቅም እንዳለው ኃላፊው ጠቅሰው፣ ገና ብዙ ያልተሠራበትና ብዙ ሊሠራበት የሚገባ ዘርፍ መሆኑን ተናግረዋል። ለዘርፉ እድገት ማነቆ ከሆኑት መካከልም ወጥ የሆነ የገበያ ዋጋ አለመኖር እና ከቆዳ ውጪ የሆኑ የዘርፉ ግብዓቶች ከውጭ የሚመጡ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ቅዱስ፤ ለኢንዱስትሪው በግብአትነት በዋናነት የሚያገለግለው ቆዳ ብቻ በአገር ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚገኝ ይናገራሉ። ከውጭ የሚመጡትን የተቀሩት ግብዓቶች ማግኘት ፈተና መሆኑን አቶ ቅዱስ ይገልጻሉ። ይህንንም አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ አብዛኛዎቹ የአንበሳ ጫማ ሶሎች እና የተለያዩ ኬሚካሎች ከውጭ አገር የሚመጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይህም አገሪቷ ካለባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር ተያይዞ የምርቶቹን ዋጋ ከፍ ያደርገዋል ብለዋል። እነዚህና ተያያዥ ምክንያቶች የቆዳ ውጤቶች ወጥ የሆነ ዋጋ እንዳይኖራቸው አድርገዋል ሲሉም ገልጸው፣ ይህም ገበያው እንዲቀዛቀዝ ማድረጉን ነው የተናገሩት።

ያም ቢሆን ግን የአገር ውስጥ ቆዳ በውጭው ዓለም እጅግ ተፈላጊ በመሆኑ ፋብሪካው የተለያዩ የቆዳ ምርቶችን በማምረት ለውጭ ገበያ እያቀረበ እንደሆነ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የአንበሳ ጫማ ፋብሪካ አብዛኛው ምርት ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነው፤ ምርቶቹም ሦስት ዓይነት ሲሆኑ፣ እነሱም ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጭምር ተደራሽ መሆን የሚችሉ ናቸው። የውጭ ገበያ መዳረሻቸውም በስፋት ማዳጋስካር ነው፤ ፋብሪካው ምርቶቹን በቀጥታ ወደ ማዳጋስካር በስፋት ኤክስፖርት ቢያደርግም፣ የማዳጋስካር ገዢዎች ምርቶቹን ወደ አሜሪካና ሌሎች አገራት ይልኳቸዋል። ካናዳ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቡሩንዲና ሩዋንዳ ምርቶቹ የሚላኩባቸው ሌሎች አገሮች ናቸው።



የኢትዮጵያ የቆዳ ውጤቶች ተፈላጊነት እያጨመረ ነው

መድረኩ የገበያ ትስስር መፍጠር ዋና ዓላማው መሆኑን አቶ ቅዱስ ጠቅሰው፣ በዚህም በንግድ ትርዒቱ ተሳታፊ ከሆኑ የውጭ አገር ገዢዎች ጋር የመተዋወቅና የገበያ ትስስር የመፍጠር አጋጣሚ እንደሚፈጥር ገልጸዋል። ቀደም ሲል አንበሳ ጫማ በጥንካሬው እንደሚታወቅና በዲዛይን ግን ክፍተት አለበት ተብሎ እንደሚታሰብ አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግን እጅግ በተሻሻሉ ዲዛይኖች መምጣቱን ለማስተዋወቅ እንደሚጠቅም ይናገራሉ።

ጥራት፣ ምቾትና ጥንካሬን በመያዝ ከውጭ ገበያ በተጨማሪ በአገር ውስጥም የአንበሳ ጫማን የዲዛይን መሻሻል ተከትሎ ምርቶቹ በስፋት ወደ ገበያው እየገቡ መሆናቸውን በማስተዋወቅ ሰፊ የገበያ ትስስር ለመፍጠር የንግድ ትርኢቱ እንደሚረዳም ተናግረዋል።

አንበሳ ጫማ የዲዛይን መሻሻል ለማምጣትና ገበያው ውስጥ ለመቆየት የተለያዩ የገበያ ጥናቶችን ማድረጉን የተጠቀሱት አቶ ቅዱስ፤ ከዚህ ቀደም ማንኛውንም ዲዛይን በፋብሪካው በማዘጋጀት ጫማውን ሠርቶ ወደ ገበያ ማውጣትና የገበያውን ሁኔታ እየተመለከቱ መልሶ የማምረትና መሸጥ አሠራርን ይከተል እንደነበር ያስታውሳሉ። አሁን የገበያ ጥናት በማድረግና ያለውን ክፍተት በማየት፣ ከደንበኞች አስተያየት በመሰብሰብ በደንበኞች ፍላጎት መሠረት እያመረተ ለገበያ እንደሚያቀርብ አስታውቀዋል።

አንበሳ ጫማ በውጭ ገበያ እጅግ ተፈላጊ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ቅዱስ፤ ተመራጭ የሚያደርገውም የመጀመሪያው የምርቶቹ ጥራትና ጥንካሬ መሆኑን ይገልጻሉ። አሁን ላይ ደግሞ ምርቶቹ በዲዛይንም ተመራጭ እየሆኑ መምጣታቸውን ተናግረዋል። በተለይም ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች ገዢዎች በሚሰጡት ዲዛይን መሠረት የሚመረቱ በመሆናቸው ፋብሪካውን ተመራጭና ተወዳጅ እንዲሆን አስችለውታል ይላሉ።

ሌላው ደንበኞች በሚፈልጉት ጊዜ አንዳንዴም ከተቀመጠው ጊዜ ቀደም በማለት ምርቶቹን ማስረከብ መቻሉ በኤክስፖርት ገበያ ውስጥ በስፋት መግባት እንዳስቻለው አመልክተዋል። አንበሳ ጫማ በከፍተኛ ካፒታል የሚንቀሳቀስና በአገሪቱ ከሚገኙ ጫማ ፋብሪካዎች መካከል ትልቁ የጫማ ፋብሪካ መሆኑ ይታወቃል።

አምሳለና ሳምራዊት የቆዳ ውጤቶች አምራች ድርጅትን ወክለው ያገኘናቸው ወይዘሮ አምሳለ ታደሰ የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን ይዘው በንግድ ትርዒቱ ላይ ለማስተዋወቅ ቀርበዋል። የንግድ ትርዒቱ ለዘርፉ መነቃቃት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ ኢንዱስትሪውን ከፍ ማድረግም ያስችላል ሲሉ ወይዘሮ አምሳለ ይናገራሉ። አጠቃላይ የቆዳ ውጤቶችን ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም በማስተዋወቅ ብዙ መሥራት እንደሚቻል ጠቅሰው፣ የንግድ ትርዒቱ ልምድ ከመለዋወጥ ባለፈ የገበያ ትስስር መፍጠር እንደሚያስችልም ነው የተናገሩት።

የአገሪቱ ቆዳ በውጭው ዓለም እጅግ ተፈላጊ እንደመሆኑ ይህን ተፈጥሮ የሰጠንን ቆዳ በቴክኖሎጂ ደግፎ አገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ውጤት ማግኘት እንድትችል መሥራት ከሚመለከታቸው ሁሉ እንደሚጠበቅ አስገንዝበዋል።

የዘመን አሞር የቆዳ ውጤቶች ኩባንያ ዲዛይነር፣ መሥራችና ባለቤት ዘመን አሞር እንደምትለው፤ ኩባንያው በዓለም ገበያ እጅግ ተወዳጅና ተመራጭ በሆነው የኢትዮጵያ «ሃይላንድ ሺፕ ስኪን» ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ ትናገራለች።

ዘመን እንዳለችው፤ በደጋማ አካባቢና ከፍታ ቦታ የሚገኙ በጎች ብርዱን ለመከላከል በተፈጥሮ እግዚአብሔር የሰጣቸው ጸጋ አለ። የበጎቹ ቆዳ በተለየ መንገድ ከጨርቅ የሳሳ ሆኖ ነገር ግን እጅግ በጣም ጠንካራ ነው። በዚሁ ተፈጥሯቸው ምክንያትም ቆዳቸው በውጭ ገበያ እጅግ ተፈላጊና ተመራጭ ነው። ነገ ደግሞ ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ይበልጥ ከፍ ማድረግ የሚችል የቆዳ ዓይነት ነው ስትል ዘመን አብራርታለች።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበርም ይህንን በዓይነቱ የተለየ የቆዳ ዓይነት በተለየ መንገድ ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ ጊዜ ወስዶ እየሠራበት መሆኑን ተናግራለች። ለአብነትም በአውሮፓ አገራት ይህ ቆዳ እንዲተዋወቅ እየተደረገ መሆኑን ዘመን ጠቅሳ፣ ወደፊት ትልቅ ተስፋ ያለውና ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ የሚችል የቆዳ ዓይነት መሆኑን አስታውቃለች። ኩባንያው ቆዳ መክበድ የለበትም ብሎ እንደሚያምን ትገልጻለች። ከቆዳው ልስላሴ የተነሳ ምርቶቹ ለማምረት እጅግ ፈታኝና አድካሚ ቢሆኑም፣ ውጤቱ ግን እጅግ ውብና ማራኪ ነው ትላለች።

እንዲህ ዓይነት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች መዘጋጀታቸውም በዋናነት የገበያ ትስስር ለመፍጠር ያስችላል ያለችው ዘመን፤ በተለይም ኢትዮጵያ አሁን ላይ ለጀመረችው ነፃ የንግድ ቀጣና ተወዳዳሪ ሆኖ ዕድሉን ለመጠቀም ትልቅ እገዛ ማድረግ እንደሚችል ነው ያስረዳችው።

በነፃ የንግድ ቀጣናው ተሳታፊ ለመሆን እንደ አገር ምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ የማየት አጋጣሚም የሚፈጥር ትልቅ ሁነት መሆኑን ተናግራለች። ከተለያዩ አፍሪካ አገራት የመጡ ገዢዎች በንግድ ትርዒቱ በቀረቡ የቆዳ ውጤቶች እጅግ ሲደሰቱና ሲገረሙ እንደነበር ያስተዋለችው ዘመን፤ ለማሳያ ያቀረበቻቸውን ምርቶችን ለመግዛት ፍላጎት እንዳሳዩ ገልጻለች።

የቆዳ ምርቶቿን ወደ አሜሪካና ካናዳ ኤክስፖርት በማድረግ እንደምትሸጥ ጠቅሳ፣ በቀጣይ ግን በነፃ ንግድ ቀጣናው ለመሳተፍ ከፍተኛ ጉጉት እንዳደረባትም ተናግራለች። በርቀት ከሚገኙት ከአሜሪካና ከካናዳ ገበያ ይልቅ እንደ ኬንያ ባሉ ጎረቤት አገራት መገበያየት መቻልና የንግድ ትስስር መፍጠር ጠቀሜታው የጎላ ነው ብላለች። ከዚህ ቀደም አፍሪካ ውስጥ ያልነበረውን ነፃ የንግድ ቀጣና በመጠቀም ለኢትዮጵያ ቅርብ በሆኑ የአፍሪካ አገራት ተጉዞ የንግድ ትስስር መፍጠር «ኬንያ ለቁርስ ሄዶ፣ ለእራት ኢትዮጵያ እንደመመለስ» ነው በማለት በነፃ የንግድ ቀጣናው ያላትን ትልቅ ተስፋ ገልጻለች።

የመላው አፍሪካ ዓለም አቀፍ የቆዳ ንግድ ትርዒት እስከአሁን ለ12 ጊዜ መካሄዱን ያስታወሱት የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር ዋና ጸሐፊ አቶ ሰለሞን ጌቱ፣ ዓለም አቀፍ በሆኑ ተግዳሮቶች ከሁለትና ሦስት ዓመታት ወዲህ ዘርፉ የገበያ መረበሽና የመቀዛቀዝ አዝማሚያ ታይቶበታል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤13ኛው የመላው አፍሪካ የቆዳ ንግድ ትርዒት መዘጋጀቱ በተከታታይ ጊዜ ከታየበት የመቀዛቀዝና የገበያ መረበሽ ለማውጣትና እንዲነቃቃ ለማድረግ ይጠቅማል። ዘርፉ የመልማትና የማደግ ሰፊ ዕድል ያለው ነው። ይህም ማለት ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ሀብት በማፍራት፣ እንዲሁም በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ተሳታፊ በማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል ዘርፍ ነው።

የንግድ ትርዒቱም ይህን ትልቅ አቅም ያለው፣ ነገር ግን ብዙ ጥቅም ላይ ያልዋለውን ሀብት ለመጠቀምና ለማነቃቃት የተዘጋጀ ነው ያሉት ዋና ጸሐፊው፣ በዘርፉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተዋናዮች ስለመኖራቸው ይናገራሉ። ከእርድ በኋላ ቆዳን ሰብስበው የሚያቀርቡ፣ የተሰበሰበውን ቆዳ አልፍተው የሚያለሰልሱ የቆዳ ፋብሪካዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ ይህን ቆዳ ተረክበው ጫማ፣ ቦርሳ፣ ቀበቶና ሌሎች የቆዳ ውጤቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በርካቶች መሆናቸውን አመልክተዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾችም ወደ ዘርፉ መጥተዋል ነው የሚሉት። ይህም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዋጋ እያጣ የመጣው የጥሬ ቆዳ ምርት ፈላጊ አንዲያገኝ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውም ጠቁመዋል።

ይህ ውጤት የመጣውም ኢትዮጵያ የአገር በቀል ኢኮኖሚን መሠረት በማድረግ ባላት ጸጋ መሥራት እንድትችል መደረጉ አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሌላው ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ወደ ተግባር ማስገባት መቻሏ ነው ይላሉ። በመሆኑም ኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪው የኢኮኖሚ ድርሻ እንዲያድግ ትልቅ አቅጣጫ ይዛ እየሠራች መሆኑ ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄም ለዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ እያረከተ መሆኑን አቶ ሰለሞን ጠቅሰዋል። የተማሪዎች ጫማና ቦርሳዎችን በአገር ውስጥ አምራቾች ማምረት መጀመሩ የቆዳ ኢንዱስትሪውን በእጅጉ እያነቃቃ እንደሆነ ተናግረው፣ ለዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክት ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ ከስድስት መቶ ሺ በላይ ጫማዎችን ማምረት መቻሉ ተጠቃሽ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዚህ ወቅትም ተዘግተው የነበሩ ትናንሽ የሚባሉ ኢንዱስትሪዎች ሁሉ ተከፍተው ትስስር መፍጠር እንደቻሉና ዘርፉም እንደተነቃቃ ነው አቶ ሰለሞን የተናገሩት። በቀጣይም በተማሪዎች ጫማ ላይ ብቻ የተመሠረተው ዕቅድ ከሰባት መቶ ሰባ ሺ በላይ አዲስ የሥራ ዕድል የሚፈጠር ይሆናል ሲሉም ጠቁመዋል። ስለዚህ ቆዳ ብዙ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፤ አይጣልም፤ ተኪ ምርትን በማምረት ከውጭ የሚገባውን ማስቀረት ይቻላል። ይህም ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚኖረው አበርክቶ የጎላ ነው ብለዋል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ዘመን አይሽሬው ብስክሌተኛ

ማሕሌት አብዱል

በዛሬው ባለውለታዎቻችን ዓምዳችን ከስፖርቱ ዓለም ጎራ ብለን ኢትዮጵያዊው ብስክሌት ጋላቢና በዘርፉ ሀገሩን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተዋወቀውን ገረመው ደንቦባን ይዘን ቀርበናል። ይህ የአገር ባለውለታ እንግዳችን የተወለደው ጣሊያን ኢትዮጵያን ከመውረሩ አንድ ዓመት በፊት አዲስ አበባ አንዋር መስጊድ ፊት ለፊት መዲና ሕንፃ የተሠራበት ቦታ መሆኑን በእርሱ ዙሪያ የተሰነዱ ጽሑፎች ያስረዳሉ። ዕድሜው ለፊደል ቆጠራ እንደደረሰም ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ግቢ ያስተምሩ በነበሩ ቄስ አማካኝነት የፊደል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ፤ በቀድሞ ሥሙ ቀበና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አሁን ኮከበ ጽብሐ እየተባለ በሚጠራው ትምህርት ቤት ገና በአሥር ዓመቱ እየተመላለሰ መማር መጀመሩንም ያመለክታሉ።

እንደመረጃው ገረመው ብስክሌት መንዳትና ማዘውተር የጀመረው ገና የሰባት ዓመት ልጅ እያለ ነው። የሚገርመው ግን በወቅቱ በእርሱ ጊዜ እንደዛሬው የልጅ ብስክሌት ባለመኖሩ ትላልቅና አጫጭር ብስክሌቶች ላይ እግሩን በፊላዮ (መሐሉ ላይ ያለው ብረት) እያሾለከ ካልሆነ በስተቀር ኮርቻው ላይ ተቀምጦ መንዳት አይችልም ነበር። ወላጅ እናቱም ልጃቸው ለብስክሌት ያለውን ፍቅርና ችሎታ እንዲሁም የትምህርት ቤቱን ርቀት በሚገባ በመረዳታቸው በ30 ብር አዲስ ብስክሌት ገዝተው ሰጡት። ገረመው ታዲያ በጊዜውም የተሰማውን ስሜት አሁንም ድረስ መግለጽ እንደማይችል ቃለመጠይቅ በተደረገለት አጋጣሚ ሁሉ ሳያነሳው አያልፍም። እናት ልጃቸው በመንገድ ርቀት እንዳይጐዳባቸው ይህን ዘዴ ሲዘይዱ ልጃቸው በብስክሌት ሀገሩንና አህጉሩን በኦሎምፒክ ይወክላል ብለው ሊገምቱ ቀርቶ አስበውትም እንደማያውቁ ግልፅ ነው።

የነገውን አምርቂ ውጤት ከወዲሁ የተነበየችለት እድሉም በአዲሷና ብርቋ ብስክሌቱ ጓደኛውን ከኋላ እያፈናጠጠ ከአሜሪካ ግቢ ተነስቶ የአቡነ ጴጥሮስን ዳገት በቮላታ ፉት ብሎት ፒያሣን አቆራርጦ በራስ መኮንን አራት ኪሎ ገስግሶ ቀበና ቀዳማይ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት በራፍ ላይ ከች ማለትን የዘወትር ፀሎት ያህል ተያያዘው። ይህም አነሰህ ብሎ ሌላ ምስኪን ጓደኛውን ከፊት ጨምሮ በጨቅላ ጡንቻው ሁለት ጓደኞቹን ይዞ መብረሩ ለጡንቻው መፈርጠም ዋንኛ መሠረት መሆኑንም የገባው ቆይቶ ነው። ከዕለት ወደ ዕለት ለዓመታት ጡንቻውንና ፍጥነቱን ያፈረጠመው ገጠመኙ ተባብረው ለመጀመሪያ ጊዜ በ1943 ዓ.ም በብስክሌት ውድድር እንዲቀርብ የልብ ልብ ሰጠው።

በውድድሩም የካበተ ልምድና ብስክሌት ካላቸው የጣሊያንና ግሪክ ተወዳዳሪዎች መሐል በዕድሜም ትንሹ ሆኖ ያገኘው የሰባተኛ ደረጃ ውጤት ይበል የሚያሰኝ ሆነለት። ያገኘው ውጤት ያስከተለለትን አድናቆት ተከትሎ ብስክሌት ልምምዱን አጠናክሮ ሲቀጥል ጉራጌዋ እናቱ ቆጮውን፣ ክትፎውን፣ ቡላውን እያቀረቡ ለውጤቱ መስመር ከጀርባው ያሉ ሁነኛ ሰው ሲደግፉት እንደነበርም ያነሳል። በ1945 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውድድሩ በስፋት ተጀመረ። በአጭር ጊዜም ከእግር ኳሱ ቀጥሎ በርካታ ተመልካቾችንና ተሳታፊዎችን በመሳብ ብስክሌት ስፖርት ስሙ ገነነ።

በኢትዮጵያ ለብስክሌት ስፖርት መጀመር ፈር ቀዳጁ ፈረደ ካሣ የተባለ ሰው ነው። ፈረደ አሥመራ ከጣሊያን ብስክሌተኞች ጋር ሲወዳደር የቆየና ቀድሞ ኦርማ ጋራዥ ወይም አውራ ጐዳና ጋራዥ የሚሠራ ነበር። ፈረደ ጐላ በ1945 ዓ.ም ከታዋቂው የስፖርት ሰው ከክቡር ይድነቃቸው ተሰማ ጋር በመነጋገር ባዘጋጀው ውድድር ገረመው ደንቦባ "ቢያጆ" በሚሰኝና ያውም በውሰት በተገኘ ብሰክሌት ለመወዳደር ተሰለፈ። ከአርባ በላይም ተወዳዳሪ በተገኘበት ፉክክር ለመጀመሪያ ጊዜ አሸነፈ። በጊዜው የነበረው ውድድር ጥንካሬንና ፍጥነትን የሚጠይቅ ነበር። ገረመው ለመጀመሪያ ድሉ የተሸለመውን 25 ብር ለእናቱ አስረከበ። በወቅቱ ታዲያ ገንዘቡ የመግዛት አቅሙ ጠንካራ ስለነበር እናቱ በደስታ ምረቃቸውን አዥጎደጎዱለት። ለመጀመሪያ ጊዜ የታያቸውንም ራዕይ "ከፍ ያለ ቦታ ያድርስህ!" ሲሉ ተመኙለት።

ወጣቱ ብስክሌት ጋላቢ በተደጋጋሚም ታላላቆቹን ልምድ ያላቸውን ሚስተር ደቦስ፣ ሚዮጂ፣ ሲኖር ኮንቲ፣ ኡስማን መሐመድ፣ ኃይሉ በየነ፣ ጫላ ወርዶፋ የመሳሰሉትን በተደጋጋሚ በማሸነፍ ትኩስ፣ አዲስና ልዩ ኃይሉን አሣየ። "ከእኔ ወዲያ ማን?" የሚለው ወኔውም ልቡን ሙሉ አደረገለት። እነ አራዳ፣ ወልወል፣ ለገሀር፣ መቻል የመሳሰሉ ክለቦችም አዲሱንና ልዩ ስፖርተኛ የግላቸው ለማድረግ የተለያዩ ማባበያዎችና ተስፋ ቃሎች አጐረፉለት። በውድድር ጊዜ የሚያሳየው ብቃት ያስደሰታቸው በአቶ ፈረደ ካሣ የሚመራው ወልወል ቡድን መሪዎች የሚማርበት ትምህርት ቤት ድረስ በመሔድ ቮልሲክ የተሰኘች ብስክሌት ሸለሙት። በዚህ ማባበያ ተስቦም ክለቡን በመወከል ከ1945 ዓ.ም እስከ 1954 ዓ.ም ባሉት አሥር ተከታታይ ዓመታት የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ሆነ።

ገረመው ደንቦባ በሀገር ውስጥ የሚያሸንፈው ቀርቶ የሚፎካከረው በማጣቱ ደብዳቤ ጽፎ ያዘጋጅና ንጉሡ



አቶ ገረመው ደንቦባ

**ገረመው ብስክሌት መወዳደሩን ቢያቆምም ነፍሱን ይማረውና እነ ዶን ጥላሁን ወልደሰንበት የመሰሉ በሞስኮ ኦሎምፒክ በፔሌግሬ (የቤት ውስጥ ውድድር) በመካፈል እስካሁን ከኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነውን ጨምሮ በርካታ ብስክሌተኞችን አፍርቷል**

ለእረፍት ወደ ቢሾፍቱ የሚሄዱበትን ዕለት ሰንበት ጠብቆ መኪናቸው የሚያልፍበት አራተኛ ክፍለ ጦር (ሪቼ) ሆኖ በመጠበቅ መኪናቸው ሲያልፍ ተከትሎ የደብረዘይትን መንገድ ተያያዘው። ዱከም ሊደርሱ ጥቂት መቶ ሜትሮች ሲቀራቸው ፍጥነቱን ጨምሮ ንጉሡን የያዘው ተሽከርካሪ አጠገብ ሲደርስ ፖስታውን ከፍ አድርጐ አሳያቸው። ገረመው በወቅቱ ስሙ በብስክሌት ከመግነን አልፎ፡-

**"ይሻልሻል …. ይሻልሻል**<br>
**ገረመው ደንቦባ ይሻልሻል**<br>
**ጥላሁን ገሠሠ ይሸኝሻል**<br>
**አበበ ቢቂላ ያገባሻል፡፡**<br>
**ገረመው ደንቦባ ከዳረሽ**<br>
**ጥላሁን ገሠሠ ከሸኘሽ**<br>
**አበበ ቢቂላ ካገባሽ**<br>
**ከሴቶቹ ሁሉ ብልጫ አለሽ....።**"

እየተባለ ከሌሎች ዕንቁ ዜጐች ጋር ሕዝባዊ ግጥም ተገጥሞ የተዘፈነለት ብቻ ሳይሆን ንጉሡ በሚያገኘው አስደሳች ውጤት በተደጋጋሚ የሸለሙት በመሆኑ ጠባቂዎቻቸው (ሮያል ጋርዱ) ከመኪናቸው አጠገብ ፔዳሉን በፍጥነት እየዘወረ የሚከተላቸውን ወጣት ስፖርተኛ ፍጥነትና ጉልበት እየተደነቁ ከመመልከት ውጪ አልተከላከሉትም። ንጉሡም መኪናው እንዲቆም አዘዙ። ጄኔራል መኮንን ደነቀም ፖስታውን ተቀብለው ለንጉሡ ሰጧቸው። ገረመው ደብዳቤውን አቀብሎ ከንጉሡ ፊት ለፊት ከብስክሌቱ ወርዶ በመቆም አቀረቀረ። ንጉሡም ቁምጣ ያደረገውን ፈርጣማ ብስክሌተኛ በአድናቆት እየተመለከቱ "… ምንድነው የምትፈልገው አንተ ጐረምሳ....?" ሲሉ ይጠይቁታል። እሱም በተረጋጋና ፍፁም ጨዋነትና ሥነ-ምግባር ያሻውን ፀባይ እና ለንጉሡ የሚገባቸውን ክብር በሚገልጽ ከአንገቱ ጐንበስ ብሎ መሬት ... መሬት እያየ ... ከዓለም የብስክሌት ተወዳዳሪዎች ጋር መፎካከር እንደሚፈልግ ነገራቸው።

ንጉሡ ለአዳዲስ ነገሮችና ሀገራቸው በሁሉም መንገድ እንድትጠራላቸው ከፍተኛ ጉጉት ስለነበራቸው ፈጥነውም "… ከቻልክ እንፈቅዳለን...!" ሲሉ ይሁንታቸውን አረጋገጡለት። በጄኔራል መኮንን ደነቀ በኩልም ቀጠሮ ተያዘለት። ገሬም ብስክሌቱን ወደኋላ አዙሮ ደስታውን ለማካፈል ወደ አዲስ አበባ ሸመጠጠ። የቀጠሮው ቀን ደርሶም በ30 ብር የገዛውን ምርጥ የጣሊያን ሙሉ ልብስ ከነሰደርያውና ከረባቱ ግጥም አድርጐ ንጉሡ ፊት ቀረበ። ንጉሡም በስደት እያሉ ስለ ኦሎምፒክ ውድድር፣ ክብርና ዝና በሚገባ ያውቁ ስለነበር ሀገራቸው የምትካፈልበትን ቀን ያብሰለስሉ ስለነበር የቀረበላቸውን ጥያቄ በቸልታና አጉል ስሜት በሚል መልኩ ለመለወጥ ባለመፈለጋቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደሚያመቻቹለት ቃል ገብተው አሰናበቱት።

ንጉሡም ቃላቸውን ሳያጥፉ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጥቁር አፍሪካ ሀገራት መሐል ነፃነቷን እንዳስጠበቀች በ1949 ዓ.ም አውስትራሊያ የምታዘጋጀውን የኦሎምፒክ ጨዋታዎች ለመካፈል ወደ ሜልቦርን ለመጓዝ ዝግጅቷን አጠናቀቀች። በዚህ አሰልጣኝ በሌለበት የብስክሌት ብሔራዊ ቡድናችን ውስጥ ነዋሪነቱን በቢሾፍቱ ያደረገው መንግሥቱ ንጉሤ፣ ተሰማ ሙሣ፣ አበበ ማሞ፣ መስፍን ተስፋዬና ፀሐየ ባሕታ ሲካተቱ፤ በማራቶን ባሻዬ ፈለቀና ገብሬ ብርቄ ተሰላፊዎች ነበሩ። የኦሎምፒክ ብሔራዊ ቡድናችን ወደ አውስትሪሊያ ለመጓዝ ሲነሳ መንግሥት ያዘጋጀለት አውሮፕላን መቀመጫ የሌለው የቡና እና የቆዳ መጫኛ ዳኮታ ነበር። ይኸው በቀዳሚው ኢትዮጵያዊው ፓይለት ካፒቴን አለማየሁ ደስታ አብራሪነት ምድርን የለቀቀው አይሮፕላን ከሰባት ቀንና ሌሊት አሰልቺ እና አድካሚ ጉዞ በኋላ ሜልቦርን ሲደርስ ስፖርተኛው ያደረገው ልምምድ ከመበላሸቱም በላይ የሁሉም ክብደት ከሚገባው በላይ ቀነሰ።

በሜልቦርን ኦሎምፒክ ተዳክሞና ተሰላችቶ ብቻ ሳይሆን ከልምምድ ርቆ የቆየው የኢትዮጵያ ቡድን ከመቶ በላይ የብስክሌት ተወዳዳሪዎች በተካፈሉበት ገረመው 24ተኛ ሲወጣ ቀሪዎቹ 35ተኛ፣ 37ተኛ እና 42ተኛ በመውጣት በቡድን ባገኙት ውጤት መሠረት ከዓለም በደረጃ ሰንጠረዥ ላይ በዘጠነኛ ለመቀመጥ ቻሉ። ይህም ውጤት እስካሁን ድረስ በሀገራችን ያልተሰበረ ሪከርድ ነው። ምናልባትም በአፍሪካ ቡድኑ ከአውስትራሊያ ሲመለስ የአውስትራሊያን ንጉሥ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በስጦታ መልክ እንዲበረከትለት የሰጠውን አንድ ወንድና አንድ ሴት ካንጋሮ ይዞ መጣ። የኦሎምፒክ ቡድኑም ቤተ-መንግሥት ቀርቦ ካንጋሮዎቹን ለንጉሡ አስረከበ። ንጉሡም ለኦሎምፒክ ልዑኩ የደረት ኒሻን ሸልመዋል።

"በኦሎምፒኩ ጨዋታ በአጨራረስ ብልጠት ውጤቱን አሳልፎ የሰጠ" በሚል ርዕስ አውስትራሊያ የሚታተም ጋዜጣ ገረመው ከፊት ሲመራ የሚያሳየውን ፎቶ አትሞ በማውጣት ለዓለም አስተዋወቀው። ከኦሎምፒክ መልስም እስራኤል የተመሠረተችበትን ሰባተኛ የነፃነት ቀን ስታከብር የክብር ተወዳዳሪ እንዲሆንላት ባደረገችለት ጥሪ መሠረት ከዓለም ምርጥ በራሪዎች ጋር ተወዳድሮ ሰባተኛ ወጣ። ከአራት ዓመት በኋላም 1952 ዓ.ም ጣሊያን በተዘጋጀው ኦሎምፒክ ገረመው ደንበባ ተካፍሏል። በውድድሩም በከፍተኛ ፍጥነት በፊት እየመራ ባለበት ጊዜ ብልጠትና ልምዱ ያላቸው ተወዳዳሪዎች ከኋላ ደርሰው ጐማውን በመግጨት መንገዱን ስቶ ከፉኛ እንዲወድቅ በማድረጋቸው እጁ ተሰብሮ ለማቋረጥ ተገደደ። ከሮም በኋላ ገረመው ኦሎምፒክን የተካፈለው በተወዳዳሪነት ሳይሆን በአሰልጣኝነት ነው - 1960 ዓ.ም ጃፓን ቶኪዮ ላይ።

ገረመው ብስክሌት መወዳደሩን ቢያቆምም ነፍሱን ይማረውና እነ ዶን ጥላሁን ወልደሰንበት የመሰሉ በሞስኮ ኦሎምፒክ በፔሌግሬ (የቤት ውስጥ ውድድር) በመካፈል እስካሁን ከኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነውን ጨምሮ በርካታ ብስክሌተኞችን አፍርቷል። የሚገርመው ደግሞ ካሉት 11 ልጆች ሶስቱ ወንዶችና አንዲት ሴት ልጁ የብስክሌት ተወዳዳሪና አፍቃሪ ነበሩ። በአሰልጣኝነት ዘመኑም ናይጄሪያ፣ ሌጐስ በተዘጋጀው የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ላይ ወርቅ ይዞ ተመልሷል። ሁለ-ገቡ ገረመው በብስክሌትም ብቻ ሳይሆን በሀገር ቤት የደጋው መኪና እሽቅድድምም ቀደምት ታሪክን የጨበጠ ነው። አመለ ሸጋው ገረመው ደንቦባ የብስክሌት ውድድሮች በሚደረጉበት ስፍራ በመገኘት ብቻ ሳይሆን ተወዳዳሪዎች ከውጪ ውድድር ሲመለሱ በመቀበል፣ ልምዱን ማካፈል፣ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስና ፕሪንቲንግ ሚዲያዎች ለቃለ-ምልልስ ሲፈለጉት ፈጥኖ በመገኘት የካበተ ልምዱን፤ ምክሩን ያስተላልፋል። ለዚህ የሀገርና የሕዝብ ባለውለታ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ከሁለት ዓመት በፊት ለገጣፎ የመሬት ስጦታ አበርክቶለታል።

የመጀመሪያው ኢትዮጵያ በተሳተፈችበት ሜልቦርን ኦሎምፒክ በብስክሌት ስፖርት ኢትዮጵያ ወክሎ በመሳተፍ እና ባንዲራዋን በኦሎምፒክ በመያዝ ቀዳሚ የሆነውና በቶኪዮ ኦሎምፒክም በዋና አሠልጣኝነት ቡድኑን በመምራት ከ30 በላይ ዋንጫ እና 32 ወርቅ ሜዳሊያ ማስመዝገብ የቻለው ይህ ድንቅ አትሌት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በ90 ዓመቱ ልክ የዛሬ ሁለት ወር በሞት ማጣታችን ይታወሳል። እኛም ይንን ድንቅ ኢትዮጵያዊ ብስክሌት ጋላቢ በእንዲህ መልኩ ልንዘክረው ወደድን።

# ስፖርት





## የትግራይ ክልል ስፖርትን ወደ እንቅስቃሴ ለመመለስ ጥረቶች ተጀምረዋል

አለማየሁ ግዛው

በትግራይ ክልል የስፖርት እንቅስቃሴዎችን ወደ ቀድሞው ለመመለስ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ተጠቁሟል። የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር የስፖርት ኮሚሽን በክልሉ ስፖርቱን ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ በመመለስ ውድድሮችን ዳግም ለማስጀመር ቁርጠኛ መሆኑን ገልጿል።

በትግራይ ክልል በጦርነት ምክንያት ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ተቋርጠው የቆዩ ሲሆን ክልሉ ከተለያዩ ውድድሮች ርቆ መቆየቱ ይታወቃል። አሁን ግን በተፈጠረው ሰላም ቆሞ የነበረው የስፖርት እንቅስቃሴ ይመለሳል ተብሎ ይጠበቃል።

ክልሉ በኢትዮጵያ ስፖርት ውስጥ የራሱ የሆነ ድርሻ ያለው መሆኑን ያስታወሱት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የስፖርት ኮሚሽን ኮምሽነር አቶ ተክላይ ፍቃዱ፣ በጦርነቱ ምክንያት በክልሉ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ከመቋረጣቸው በፊት በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ሰፊ ተሳትፎ ይደረግ እንደነበር ይናገራሉ። ክልሉ በስፋት ከሚሳተፍባቸው የስፖርት ዓይነቶች መካከል እግር ኳስ፣ አትሌቲክስና ብስክሌት ዋንኞቹ ናቸው። እነዚህን ወደ ተለመደው እቅስቃሴያቸው ለመመለስም የክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ሥራዎች መጀመሩን አቶ ተክላይ ጠቁመዋል።

ከጥቂት አመታት በፊት የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ዋንጫን ማንሳት ከቻለው መቐለ ሰባ እንደርታ ጀምሮ እንደ ሽሬ እንደሥላሴ፣ ውልዋሎ አዲግራት ዩኒቨርሲቲና ሌሎች በከፍተኛ ሊግና በክልል ክለቦች ቻምፒዮና የሚሳተፉ ክለቦች በጦርነቱ ሳቢያ ከውድድር ርቀው ቆይተዋል።



አቶ ተክላይ ፍቃዱ፣

በተለይም በትልቁ የፕሪሚየር ሊግ ውድድር በመሳተፍ ላይ የነበሩት ሦስቱ የክልሉ ክለቦች መቐለ ሰባ እንደርታ፣ሽሬ እንደሥላሴና ውልዋሎ አዲግራት ዩኒቨርሲቲ በ2016 ወደ ውድድር እንዲመለሱ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አቶ ተክላይ አስረድተዋል። ክለቦቹ ወደ ውድድር እንዲመለሱ ውሳኔው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ቢሆንም የክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ክለቦቹን በቀጣይ ዓመት ወደ ውድድር የመመለስ ሃሳብ እንዳለውም አክለዋል።

ክለቦቹ ከዚህ በፊት የነበሩበትን ደረጃና የደረሰውን ውድመት አጥንተው መጨረሳቸውን የጠቀሱት አቶ ተክላይ፣ ክለቦቹ እንዴት ወደ ፕሪሚየር ሊጉ ይመለሱ የሚለው ጥያቄ መነሳቱንም ጠቅሰዋል።

በክልሉ አሁን ባለው ሁኔታ መሠረተ ልማቶች መውደማቸውና ኳስ ተጫዋቾች ከመደበኛ የስፖርት እንቅስቃሴ በመውጣታቸው እንዴት ወደ እንቅስቃሴ ይመለሱ በሚለው ጉዳይ ላይ ከብሔራዊ ስፖርት ፌዴሬሽኖች ጋር ውይይቶች እየተደረጉ እንደሆነም ተጠቁሟል።

በጦርነቱ ከደረሰው ጉዳት አንጻር ክለቦችን ወደ ውድድር ለመመለስ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ስለሆነ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በጋራ መሥራት እንደሚያስፈልግ የገለፁት አቶ ተክላይ፣ በዚህም መሠረት ከእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ ጋር እንዴት እናስጀመር በሚለው ውይይት ለማድረግ እቅድ መኖሩን ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ተክላይ ገለፃ፣ በአትሌቲክሱም ወደ እንቅስቃሴ ለመመለስ ስፖርት ኮሚሽኑ ጥረት በማድረግ ላይ ነው። በክልሉ የሚገኙ የማሰልጠኛ ማዕከላት ላይ ጉዳት ከመድረሱም በተጨማሪ ሰልጣኞች መበታተናቸው እንዲሁም በዕድሜ ምክንያት እንደ አዲስ ምልመላ ማድረግም ያስፈልጋል። ‹‹የማሰልጠኛ ማዕከላትን ዳግም እንቅስቃሴ ለማስጀመር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና ከዓለምአቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ድጋፍ ያስፈልጋል›› ሲሉም ተናግረዋል።

የክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በመጪው ግንቦት መጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤውን በማድረግ የተጓደሉ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እንዴት መሟላት እንዳለባቸው ለመወሰን እቅድ እንዳለም ታውቋል።

ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ተክላይ፣ አትሌቲክሱን ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ ለማስገባት ጥረቶች በመደረግ ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል። በዚህም ክልሉ በ52ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የመሳተፍ ፍላጎት እንዳለ ገልፀዋል። ብሔራዊ ፌዴሬሽኑም ያለውን ነገር ተመልክቶ መልስ እንደሚሰጥ ይጠበቃል።

ሌላኛው ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ ለመመለስ ጥረት የሚደረግበት የብስክሌት ስፖርት ሲሆን፣ ብስክሌት በክልሉ በርካታ ተሰጦ ያለበትና ስመጥር ስፖርተኞችን ማፍራት የቻለ ነው። የብስክሌት ስፖርትን ዳግም ወደ እንቅስቃሴ ለማስገባት በፊት ያለበት ደረጃና የደረሰውን ጉዳት በኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን ጥናቶች ተጠንቶ መጠናቀቃቸው ተጠቁሟል። በንብረት፣ የሰው ኃይልና ሌሎች ቆጠራና ልየታ መደረጉንና ውጤቱ ወደ ፊት እንደሚገለጽም ኃላፊው አስረድተዋል። ስፖርቱን ባለው ሀብት ወደ እንቅስቃሴ ለማስገባት ከኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን ጋር መስማማታቸውንም አክለዋል።

አቶ ተክላይ ከደረሰው ጉዳት አኳያ የተወሰነ ድጋፍን በማድረግ ብቻ ስፖርቱን ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ መመለስ አስቸጋሪ መሆኑን ጠቅሰው፣ የክልሉን ስፖርት ለማነቃቃት ‹‹ከጎናችሁ ነን›› በማለት ድጋፍ ላደረጉ አካላት ምስጋና አቅርበዋል። በተለይም አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ቀድሞ ክልሉን ስለጎበኘና ጉዳቱን ተመልክቶ ድጋፎችን ስላደረገ ሊመሰገን እንደሚገባው ተናግረዋል። ሁሉም የስፖርት አካላት ቦታው ድረስ በመምጣትም የደረሱ ጉዳቶችን ተመልክቶ ስፖርቱ በቶሎ ወደ እንቅስቃሴ እንዲገባ የድርሻቸውን እንዲወጡም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ንብረቶች የሆኑ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የሰጡባቸውን ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ንብረቶች (የተሽከርካሪ ጎማዎች፣ ባትሪዎች፣ ከነመዳሪዎች፣ ቸርኬዎች፣ ፍላፖች፣ በርሜሎች፣ የቢሮ መገልገያ ፈርኒቸሮች እና የተለያዩ የሕክምና ዕቃዎች) ባሉበት ሁኔታ አወዳድሮ በግልፅ ጨረታ ለመሸጥ ይፈልጋል።

1. ተጫራቾች ሜክሲኮ ሰንጋ ተራ ዮቤክ የንግድ ማዕከል ህንፃ ላይ በሚገኘው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት 6ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 606 በመምጣት የተለያዩ ተቋማት በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የሰጡባቸውን ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች፣ ንብረቶች (የተሽከርካሪ ጎማዎች፣ ባትሪዎች፣፣ ከነመዳሪዎች ቸርኬዎች፤ ፍላፖች፣ በርሜሎች፣ የቢሮ መገልገያ ፈርኒቸሮች እና የተለያዩ የሕክምና ዕቃዎች) ዝርዝርና ብዛት የያዘ የጨረታ ሰነድ ለተሽከርካሪዎች የማይመለስ ብር 400.00/አራት መቶ ብር/ ሌሎች ንብረቶች የተሽከርካሪ ጎማዎች ባትሪዎች ከነመዳሪዎች ቸርኬዎች፤ ፍላፖች፣ በርሜሎች፣ የቢሮ መገልገያ ፈርኒቸሮች እና የተለያዩ የሕክምና ዕቃዎች የማይመለስ ብር 300.00/ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተገኝተው መግዛት ይችላሉ።
2. በዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ተጫራቹ የሰጠው ዋጋ በሚለው አምድ ስር ዋጋ በአሃዝ እንዲሁም በፊደል ያለ ስርዝ ድልዝ ገልጸው በታሸገ ኤንቨሎፕ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 708 ለዚሁ ሥራ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 የስራ ቀናት ውስጥ ቅዳሜን ጨምሮ ተገኝተው ማስገባት አለባቸው።
3. ተጫራቾች በአሃዝና በፊደል እንዲሁም በነጠላና በጥቅል በሰጡት ዋጋ መካከል ልዩነት ካለ አገልግሎቱ ከፍተኛውን ዋጋ ወስዶ ያወዳድራል።
4. ተጫራቾች ትክክለኛ አድራሻቸውንና ስማቸውን በመግለጽ በመጫረቻ ሠነዳቸው ላይ መፈረም አለባቸው::
5. ተጫራቾች ለሽያጭ የተዘጋጁትን የተሽከርካሪ ጎማዎች ፣ባትሪዎች፣ ከነመዳሪዎች፣ ቸርኬዎች፣ ፍላፖች፣ የአንዱን መስሪያ ቤት ሎት/ምድብ/ በጥቅል መጫረት አለባቸው።በርከክብ ወቅትም መርጦ መውሰድ አይቻልም::
6. ተጫራቾች ለሚገዙት ተሽከርካሪ የጨረታ መነሻ ዋጋውን 20 በመቶ (20%) ሌሎች ንብረቶችን የጨረታ መነሻ ዋጋውን 10 በመቶ (10%) የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አሰርተው ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር በማያያዝ ሳጥኑ ውስጥ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ማስገባት ይኖርባቸዋል። የሚዘጋጀው የጨረታ ማስከበሪያ ዋጋ ሲ.ፒ.ኦ. ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ከሆነ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ብቻ መሆን ይኖርበታል።
7. ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን በ16ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ በ4:00 ሰዓት ተዘግቶ በዚያኑ ቀን በ4:15 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መሰብሰቢያ አዳራሽ 9ኛ ፎቅ ይከፈታል። ሆኖም የጨረታ መከፈቻ ቀኑ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከላይ በተገለጸው ሰዓት ይከፈታል።
8. ተጫራቾች በራሳቸው ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኙ በመቅረታቸው የጨረታውን አከፋፈት አያስተጓጉልም::
9. ተሽከርካሪዎች የነበረባቸው የቦሎ ዕዳ እና የስም ዝውውር ወጪ በአሸናፊው ተጫራቾች ይሸፈናል::
10. አንድ ተጫራች አንድ ተሽከርካሪ እና ከአንድ ምድብ ንብረቶች በላይ መግዛት ይችላል። ሆኖም አንድ ተጫራች ለአንድ ተሽከርካሪ፤ ለአንድ ምድብ ንብረት የተለያየ ዋጋ በመስጠት መወዳደር አይችልም::
11. በመነሻ ዋጋና በታች የቀረበ ዋጋ ተቀባይነት የለውም::
12. የጨረታ ሳጥን ከተዘጋ በኋላ ኮድ ወይም መለያ ቁጥር ስጽፍ ተሳስቻለሁ ወይም ሳልጽፍ ቀርቻለሁ የሚሉ ጥያቄዎች ተቀባይነት የላቸውም::
13. ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ተካፋይ ሆኖ ጨረታው ከተዘጋ በኋላ ከጨረታው መውጣት ወይም የሰጠውን ዋጋ ማሻሻል ወይም መለወጥ አይችልም::
14. የጨረታ ሳጥን ከታሸገ በኋላ የሚመጡ ማናቸውም ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም::
15. ተጫራቹ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ንብረቱ የሚገኝበት ተቋም ድረስ በመሄድ ንብረቱን አይተው መጫረት ያለባቸው ሲሆን ንብረቱን ሳያዩ ቢጫረቱ ግን ለሚፈጠረው ቅሬታ/ችግር አገልግሎቱ ኃላፊነቱን አይወስድም:፡

**ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በስልክ ቁጥር** 011-557-31-76 ወይም 011-557-32-35 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ

አገልግሎቱ የተሻለ መንግድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት**